# የግብረገብ ትምህርት
# የመምህር መምሪያ
# 6ኛ ክፍል


ተርጓሚዎች

ሞቲ ድንቁ

ኃይሉ ብሩ

ተስፋዬ አበባየሁ

ገነት ከዲር

አርታኢዎች

አንበሴ በቀለ
እሸቱ አጋ

ግራፍክስ

ታደሰ ድንቁ

ገላጭ ሥዕል

ብዙአየሁ ግርማ

ገምጋሚ

ደረጀ መኮንን

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2015/2023

ይህ የመምህራን መምሪያ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በ2015/2023 ተስማምቶ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው። የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

ይህን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ በየትኛውም መልኩ ማሳተምም ሆነ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

## ምስጋና

ይህ የመምህራን መምሪያ በትምህርት ሚኒስቴር አመራርት በሀዋሳ ፣ጅማ፣ አዲስ አበባና ባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው፡፡ በመቀጠል በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ቅንጅት ተተርጉሞና ተስማምቶ ተዘጋጀ፡፡

በመሆኑም በዚህ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው የትምህርት ሚኒስቴር፣ የዩኒቨርስቲ አዘጋጆችና በክልላችን ላሉ ተርጓሚዎችና አስማሚ ባለሙያዎች በሙሉ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ላቅ ያለ ምስጋና አለው፡፡

# ማውጫ


ምዕራፍ 1፡ የታማኝነት መርሆች ..... 1

ትምህርት 1.1. የታማኝነት መርሆች ምንነት ..... 1

ትምህርት 1.2. የታማኝነት መርሆች ባህሪያት ..... 4

ትምህርት 1.3. የታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት ..... 7

ትምህርት 1.4. የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎች ባህሪያት ..... 9

ትምህርት 1.5. የታማኝነት መርሆችን ባለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች ..... 12

ምዕራፍ 2 ፡ ሕግን ማክበር ..... 16

ትምህርት 2.1. ሕግ የማክበር ምንነት ..... 16

ትምህርት 2. 2. ሕግ የማክበር አስፈላጊነት ..... 19

ትምህርት 2.3. የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያት ..... 21

ትምህርት 2.4. ሕግ አለማክበር የሚያስከትላቸው ችግሮች ..... 24

ምዕራፍ 3፡ መልካም ስነምግባር ..... 28

ትምህርት 3.1. የመልካም ስነምግባር ምንነት ..... 28

ትምህርት 3.2. የመልካም ሰው ባህሪ መገላጫዎች ..... 31

ትምህርት 3.3. የመልካም ስነምግባር አስፈላጊነት ..... 34

ትምህርት 3.4. የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶች ..... 36

ትምህርት 3.5. በመልካም ስነምግባሮች መጓደል የሚከሰቱ ችግሮች ..... 39

ምዕራፍ 4፡ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ..... 43

ትምህርት 4.1. የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ምንነት ..... 43

ትምህርት 4.2. የዜግነት (የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት) ውስጥ መሳተፍ ..... 46

ትምህርት 4.3. ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደት (ባህላዊ ፍርድ ቤት) ..... 48

ትምህርት 4.4 የመረዳጃ ማህበራት/ተቋማት ማጠናከር (ቡሳ-ጎኖፋ) ..... 51

ትምህርት 4.5. ኢኮኖሚ እንቅስቃሴን የሚያጠናክሩ ተቋማት (ቁጠባና ግብር) ..... 54

ምዕራፍ 5፡ የሀገር ፍቅር ...... 58
ትምህርት 5.1. የሀገር ፍቅር ምንነት ...... 58
ትምህርት 5.2. የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎች ...... 61
ትምህርት 5.3. የሀገር ፍቅር አስፈላጊነት ...... 64
ትምህርት 5.4. የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ባህሪያት ...... 66
ትምህርት 5.5. ሀገር መውደድ ...... 68
ምዕራፍ 6፡ ሰላምና ህብረት ...... 73
ትምህርት 6.1. የሰላም ምንነት ...... 73
ትምህርት 6.2 ህብረት ...... 76
ትምህርት 6.3. በሰላምና በህብረት መካከል ያለው ግንኙነት ...... 78
የ6ኛ ክፍል ግብረገብ ሲሌበስ ...... 82

## ምዕራፍ 1፡ የታማኝነት መርሆች

### መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የታማኝነትን ምንነት፣ ባህሪያት፣ የታማኝነት መርሆች አስፈላጊነትና የታማኝነት መርሆችን ሥራ ላይ አለማዋል የሚያስከትሉትን ችግሮች በውስጡ የያዘ ነው። ከላይ የተጠቀሱትን ይዘቶች በተማሪዎች በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ያለውን ሚና ያሳያሉ። በዚህም ተማሪዎች በቤተሰቦቻቸው፣ በአካባቢያቸውና በትምህርት ቤታቸው ከእያንዳንዳቸው የሚጠበቀውን የታማኝነት መርሆች በመተግባር ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በማድረግ የምዕራፉን ትምህርት በተማሪዎች ላይ ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ይጠበቅቦታል።

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች**

- ☞ የታማኝነት መርሆችን መግለጽ፤
- ☞ የታማኝነት መርሆችን መዘርዘር፤
- ☞ የታማኝነት መርሆች አስፈላጊነትን ማብራራት፤
- ☞ የታማኝነት መርሆች ባህሪያትን በተግባር ማሳየት፤
- ☞ የታማኝነት መርሆችን አለመተግበር የሚያስከትሉትን ችግሮች መለየት።

**🕐 ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ ብዛት 19**

**☞የምዕራፉ ይዘቶች**

ትምህርት 1.1: የታማኝነት መርሆች ምንነት፤

ትምህርት 2.2: የታማኝነት መርሆች ባህሪያት ፤

ትምህርት 3.3: የታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት፤

ትምህርት 4.4: የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎች ባህሪያት፤

ትምህርት 5.4: የታማኝነት መርሆች ባለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች።

### ትምህርት 1.1. የታማኝነት መርሆች ምንነት

**ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች**

- ☞ የታማኝነት መርሆች ምንነትን ይገልፃሉ፤
- ☞ የታማኝነት መርሆች እሴቶችን ይለያሉ፤
- ☞ የታማኝነት መርሆችን ጥቅም ይዘርዝራሉ።

🕐 **ለዚህ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት 2**

**አጠቃላይ ገለፃ**

ታማኝነት ማለት ያለንን መልካም ሥነምግባር እና እሴቶች በተግባር ማሳየት እንደሆነ ማስረዳት አስፈላጊ ነው:: እንዲሁም፣ የታማኝነት መርሆች ከሚባሉት መካከል ጥቅቶቹ፡ አለመኮፈስ፣ ኃላፊነትን መወጣት፣ ቋሚ ባህሪያትን ማሳየት፣ ቁርጠኝነት፣ ለሰዉ ማሰብ መቻል እና የመሳሰሉት መሆናቸውን ለተማሪዎቹ ያስረዱ::

ይህ ትምህርት ተማሪዎች የታማኝነት መርሆችን ምንነት እንዲያውቁ እና በተግባር እንዲያሳዩ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው:: መምህር፣ እያንዳንዱ ተማሪ የታማኝነት መርሆችን በተመለከተ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የታማኝነት መርሆችን በክፍል ውስጥ እንዲወያዩበት እና ልምድ እንዲለዋወጡ ያበረታቷቸው::

ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት እንዲገነዘቡ እነዚህን ጽንሰ-ሀሳቦች ለተማሪዎቹ ማስተዋወቅ እና ይዘቱን ግልጽ በማድረግ ተዛማጅ ምስሎችን እና ምሳሌዎችን በመጠቀም ሊደግፏቸው ይገባል::

የመማር ማስተማር ዘዴ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

→ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ **ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች**

መምህር፣ በክፍል ውስጥ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ::

- ☞ የመረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ☞ አጭር ገለጻ ማድረግ
- ☞ ጥያቄ እና መልስ ማካሄድ
- ☞ የቡድን ውይይት

☞ **ቅድመ ዝግጅት**

ለመማር ማስተማር ሂደት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ያዘገጁ:: በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ ለተማሪዎች የሚረዱ ዋና ዋና ነጥቦችን ያዘጋጁ:: በተጨማሪም

ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱትን የመጣቀሻ መጽሃፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ አለቦት፡፡

☞ የመማር ማስተማር ሂደት

**1. መግቢያ**

- ☞ የታማኝነት መርሆችን ምንነት ለተማሪዎቹ አጠር ባለ አገላለፅ ማቅረብ አለቦት፤
- ☞ የዚህን ትምህርት የመማር ውጤቶች ለተማሪዎች ይግለፁ፣
- ☞ ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት እንዲረዱ የግንዛቤ ጥያቄ ማቅረብ አለቦት፤
- ☞ የተማሪዎችን በጥልቀት የማሰብ ክህሎት የሚያዳብሩ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

- ☞ የታማኝነት መርሆችን ምንነት በምሳሌ በማስደገፍ አጭር መግለጫ ለተማሪዎቹ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ይጀምሩ፡፡
- ☞ የሚከተሉትን የታማኝነት ዋና መርሆችንና የትምህርቱን ይዘት ማብራራት አስፈላጊ ነው፡፡ እነሱም፡- ታማኝነት፣ አለመኮረጅ፣ ኃላፊነትን መወጣት፣ ቋሚ ባህሪያትን ማሳየት፣ ቁርጠኝነት፣ ለሰው ማሰብ መቻል እና የመሳሰሉትን መጥቀስ አለቦት፡፡

**3. ማጠቃለያ**

- ☞ በታማኝነት መርሆች ውስጥ የተገለጹትን ዋና ሃሳቦች በመከለስ የእለቱን ትምህርት ማጠናቀቅ ይችላሉ፡፡

**4. ክትትል እና ግምገማ**

**ሀ) ክትትል**

ተማሪዎች የታማኝነት መርሆችን ምንነት እንዲረዱ፣ ወደ ኋላ ተመልሰው ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ እና ግንዛቤያቸውን በመከተል ግብረ መልስ እንዲሰጡ አበረታቷቸው፡፡

**ለ) ግምገማ**

- ☞ ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት መረዳታቸውን ለማረጋገጥ፣ የክፍል ስራ በመስጠት ወይም ቡድን በማደራጀት በታማኝነት መርሆች ምንነት ላይ እንዲወያዩ በማደረግ በምላሾቻቸው ላይ በመመስረት የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ፡፡
- ☞ በተጨማሪም የተለያዩ ምሳሌዎችን እየጠቀሱ እንዲወያዩ በማድረግ መገምገም ይችላሉ፡፡

የተግባር ጥያቄዎች  መልስ

**ተግባር 1.1**

1) ታማኝነት ማለት የግለሰብን በጎነት እና እሴት በተግባር ላይ ማዋል ነው።
2) ከታማኝ ሰው ባህሪያት ጥቂቶቹ፡-
   - አለመኮረጅ፣ ኃላፊነትን መወጣት፣ ቋሚ ባህሪያትን ማሳየት፣ ቁርጠኝነት፣ለሰው ማሰብ መቻል እና የመሳሰሉት ናቸዉ።
3) የታማኝነት መርሆች የተላበሰ ሰው ባህሪ፡-
   - እውነትን የሚናገሩ፤
   - ስህተቶቻቸውን የሚያምኑ፤
   - ቃል ኪዳኖችን የሚጠብቁ፤
   - የትምህርት ቤቱን ንብረት የሚከባከቡ፤
   - አረጋውያንን የሚረዱ፤
   - ስህተትን የሚጸየፉ።

## ትምህርት 1.2. የታማኝነት መርሆች ባህሪያት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

- የታማኝነት መርሆች ባህሪያትን ይገልፃሉ፤
- የታማኝነት መርሆችን ባህሪያት በተግባር ያሳያሉ።

**የትምህርቱ ይዘት**

1. የታማኝነት መርሆች ባህሪያት

🕐 **ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ ብዛት 6**

**አጠቃላይ ገለፃ**

ይህ ትምህርት ተማሪዎች የታማኝነት መርሆች ባህሪያትን እንድላበሱ ለማድረግ የተዘገጀ ነው። ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት እንዲገነዘቡ ለመርዳት የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ለተማሪዎቹ ማስተዋወቅ እና ይዘቱን ግልጽ በማድረግ ተዛማጅ ምስሎችን እና ምሳሌዎችን በመጠቀም ሊደግፋቸው ይገባል። መምህር፣ እያንዳንዱ ተማሪ በታማኝነት መርሆች ባህሪያት ላይ እንዲወያዩ በማድረግ ልምድ እንዲለዋወጡ ሁኔታዎችን ያመቻቹ። ለተማሪዎች የታማኝነት መርሆች ባህሪያትን አንዳንድ ምሳሌዎች በማንሳት ለምሳሌ እንደ፡- ታማኝነት፣

ቆራጥነት፣ ራስን መግዛት፣ እብሪተኛ አለመሆን፣ ኃላፊነት መወጣት፣ ወጥነት እና የመሳሰሉት መሆናቸውን ለተማሪዎች ማስረዳት ይጠበቅቦታል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ➔ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ **ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች**

መምህር በክፍል ውስጥ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ☞ የግናዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ☞ አጭር ገለጻ ማድረግ
- ☞ ጥያቄ እና መልስ ማካሄድ
- ☞ የቡድን ውይይት

☞ **ቅድመ ዝግጅት**

ለመማር ማስተማር ሂደት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና ለተማሪዎች የሚረዱ ዋና ዋና ነጥቦችን ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱትን የመጣቀሻ መጽሃፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ አለቦት፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

1. **መግቢያ**
   - ☞ የታማኝነት መርሆችን ባህሪያት ለተማሪዎቹ አጠር ያለ ማብራሪያ ይስጡ፤
   - ☞ የትምህርቱን የመማር ውጤቶች ለተማሪዎች ይግለፁ፣
   - ☞ ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት እንዲረዱ የግንዛቤ ጥያቄ ያቅርቡ፤
   - ☞ የተማሪዎችን በጥልቀት የማሰብ ክህሎትን የሚያዳብሩ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡
2. **የትምህርቱ አቀራረብ**
   - ☞ የታማኝነት መርሆችን በምሳሌ በማስደገፍ አጭር መግለጫ ለተማሪዎቹ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ይጀምሩ፡፡
   - ☞ የታማኝነት ባህሪያት እና ዋና የትምህርቱን ይዘት ማብራራት ይስጡ፡፡ እነሱም፡- ታማኝነት፣ አለመኮፈስ፣ ኃላፊነትን መወጣት፣ ቋሚ ባህሪያትን ማሳየት፣ ቁርጠኝነት፣ ለሰዉ ማሰብ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ አለቦት፡፡

**3. ማጠቃለያ**

በታማኝነት መርሆች ባህሪያት ውስጥ የተገለጹትን ዋና ሃሳቦች በመከለስ የእለቱን ትምህርት ማጠናቀቅ ይችላሉ፡፡

**4. ክትትል እና ግምገማ**

**ሀ) ክትትል**

ተማሪዎች የታማኝነት መርሆች ባህሪያትን እንዲገነዘቡ ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን በመከተል አዎንታዊ ግብረመልስ በመስጠት አበረታቷቸው፡፡

**ለ) ግምገማ**

ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት መረዳታቸውን ለማረጋገጥ፣ የክፍል ስራ በመስጠት ወይም በቡድን በማደራጀት በታማኝነት መርሆች ባህሪያ ላይ እንዲወያዩ በማደረግ በምላሾቻቸው ላይ በመመስረት የተማሪን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ፡፡

በተጨማሪም የተለያዩ ምሳሌዎችን እየጠቀሱ እንዲወያዩ በማድረግ መገምገም ይችላሉ፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 1.2**

1. የታማኝነት መርሆች ባህሪያ የሚባሉት፡- ታማኝነት፣ አለመኮፈስ፣ ኃላፊነትን መወጣት፣ ቋሚ ባህሪያትን ማሳየት፣ ቁርጠኝነት፣ ለሰዉ ማሰብና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ስለዚህ የታማኝነት መርሆችን የሚከተሉ ሰዎች የተጠቀሱትን ባህሪያት ያሳያሉ፡፡
2. ወጥነት ያለው ባህሪ ማሳየት፡- ወጥነት ያለው ባህሪ ያለዉ ሰው በግልም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ ተመሳሳይ ባህሪን የሚያሳይ ነው፤ ከጥቅም አንፃር ባህሪያቸው የማይለዋወጥ ማለት ነው፡፡
3. በክፍል ውስጥ ሊኖራችሁ ከሚገቡ የታማኝነት መርሆች ባህሪያት መካከል ጥቅቶቹ፡-
   - እውነትን መናገር፤
   - መምህራንን ማክበር፤
   - ሥራቸውን በሰዓቱ እና በትጋት ማከናወን፤
   - የትምህርት ቤቱን ንብረት መንከባከብ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ትምህርት 1.3. የታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

- ☞ የታማኝነት መርሆዎች አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፤
- ☞ የታማኝነት መርሆችን አስፈላጊነት ይገልጻሉ፤
- ☞ የታማኝንት መርሆች ለሰዎች ያለውን ጥቅሞች ያደንቃሉ፡፡

🕐 ለዚህ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት 4

የትምህርቱ ይዘት

1) የታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት

አጠቃላይ ገለፃ

ይህ ትምህርት በታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ተማሪዎች በግልም ሆነ በህብረተሰብ ውስጥ ስለ ታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ አበረታቷቸው፡፡ በተጨማሪ ምሳሌዎችን በመስጠት የትምህርቱን ይዘት እንዲረዱ ያግዟቸው፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ➔ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

መምህር፣ በክፍል ውስጥ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ☞ አጭር ገለጻ ማድረግ
- ☞ ጥያቄ እና መልስ ማካሄድ
- ☞ የቡድን ውይይት

**ቅድመ ዝግጅት**

ለመማር ማስተማር ሂደት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና ለተማሪዎች የሚረዱ ዋና ዋና ነጥቦችን ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱት የመጣቀሻ መጽሃፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ አለቦት፡፡

## የመማር ማስተማር ሂደት

### 1. መግቢያ

- ☞ የታማኝነት መርሆችን አስፈላጊነት አጠር ያለ ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጡ፤
- ☞ የትምህርቱን የመማር ውጤቶች ለተማሪዎች ይግለፁ፣
- ☞ ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት እንዲረዱ የግንዛቤ ጥያቄ ማቅረብ አለቦት፤
- ☞ የተማሪዎችን በጥልቀት የማሰብ ክህሎትን የሚያዳብሩ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- ☞ የታማኝነት መርሆችን አስፈላጊነት በምሳሌ በማስደገፍ አጭር መግለጫ ለተማሪዎቹ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ይጀምሩ፡፡
- ☞ በተጨማሪም የታማኝነት መርሆች ለግለሰብም ሆነ ለመላው ማህበረሰብ ያለውን አስፈላጊነት ለተማሪዎቹ በደንብ ማስረዳት አለቦት፡፡

### 3. ማጠቃለያ

- ☞ በታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት ውስጥ የተገለጹትን ዋና ሃሳቦች በመከለስ የእለቱን ትምህርት ማጠናቀቅ ይችላሉ፡፡

### 4. ክትትልና ግምገማ

**ሀ) ክትትል**

ተማሪዎች የታማኝነት መርሆችን አስፈላጊነት እንዲረዱ ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን በመከተል አዎንታዊ ግብረመልስ በመስጠት ማበርታታት አለቦት፡፡

**ለ) ግምገማ**

ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት መረዳታቸውን ለማረጋገጥ፣ የክፍል ስራ፣ የቡድን ሥራ በመስጠት ወይም ቡድንን በማደራጀት በታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት ላይ እንዲወያዩ በማደረግ በምላሾቻቸው ላይ በመመስረት የተማሪዎች ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ምሳሌዎችን እየጠቀሱ እንዲወያዩ በማድረግ መገምገም ይችላሉ፡፡

## የተግባር ጥያቄዎች መልስ

**ተግባር 1.3.**

1. አይደለም፡፡ መ/ር/ት፡- ምክንያቱን የጉዳይ ጥናቱን በመመረኮዝ አብረሩላቸው፡፡
2. አታሚላም፡፡ መ/ር/ት፡- ምክንያቱን የጉዳይ ጥናቱን በመመረኮዝ አብረሩላቸው፡፡

ተግባር 1.4.

1. የታማኝነት መርሆች ብዙ ጥቅሞች አሉት።
   - ማህበራዊ ግንኙነቶችን ያጠናክራል፤
   - ማህበራዊ ልማትን ያፋጥናል፤
   - ችግሮችን የመፍታት ችሎታን ያዳብራል፤
   - በሌሎች ሰዎች ዘንድ አመኔታና አክብሮት ያስገኛል።
2. የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ መኖራቸው ምን ጥቅሞች አሉት?
   - በማህበረሰቡ መካከል መተማመንን ያጠናክራል፤
   - እርስበርስ መደጋገፍና መረዳዳትን ያበረታታል፤
   - ህብረተሰቡ በመከባበር አብሮ እንዲኖር ያበረታታል።
3. የታማንነት መርሆችን በክፍል ውስጥ መተግበር ምን ጥቅሞች አሉት?
   - ተማሪዎች ለመምህራን እንዲታመኑ ያደርጋል፤
   - በተማሪዎች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፤
   - በተማሪዎች መካከል  የመረዳዳት ስሜት ይፈጥራል።

## ትምህርት 1.4. የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎች ባህሪያት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡

- የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎች ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፤
- የታማኝነት መርሆችን በተግባር ያሳያሉ።

ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት 3

**የትምህርቱ ይዘት**

1) የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎች ባህሪያት

**አጠቃላይ ገለፃ**

ይህ ትምህርት የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎች ባሕርያት ላይ ያተኩራል። መምህር፣ በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ እንዲያንጸባርቁ ማበረታታት አለብዎት።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

- ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

መምህር፣ በክፍል ውስጥ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ☞ አጭር ገለጻ ማድረግ
- ☞ ጥያቄ እና መልስ ማካሄድ
- ☞ የቡድን ውይይት

**ቅድመ ዝግጅት**

ለመማር ማስተማር ሂደት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና ለተማሪዎች የሚረዱ ዋና ዋና ነጥቦችን ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱትን የማጣቀሻ መጽሃፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ አለብዎት፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

1. መግቢያ
   - ☞ የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎችን ባሕርያት ለተማሪዎቹ አጠር ባለ አገላለፅ ያቅርቡ፤
   - ☞ የትምህርቱን የመማር ውጤቶች ለተማሪዎች ይግለፁ፣
   - ☞ ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት እንዲረዱ የግንዛቤ ጥያቄ ያቅርቡ፤
   - ☞ የተማሪዎችን በጥልቀት የማሰብ ክህሎት የሚያዳብሩ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡
2. የትምህርቱ አቀራረብ
   - ☞ የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎችን ባሕርያት በምሳሌ በማስደገፍ አጭር መግለጫ ለተማሪዎቹ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ይጀምሩ፡፡
   - ☞ መምህር፣ በተጨማሪም ከዚህ ርዕስ ጋር የሚዛመዱት ሌሎች ምሳሌዎችን በማንሳት ተማሪዎች እንዲወያዩባቸው ያድርጉ፡፡

1. ማጠቃለያ
   - ☞ የታማኝነት መርሆች የተላበሱ ሰዎችን ባሕርያት በማስመለከት ዋና ዋና ሃሳቦች በመከለስ የእለቱን ትምህርት ማጠናቀቅ አለቦት፡፡

## 2. ክትትልና ግምገማ

ሀ) ክትትል

ተማሪዎች የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎችን ባሕርያት እንዲረዱ እና ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን በመከተል አዎንታዊ ግብረመልስ በመስጠት ማበርታታት አለቦት።

ለ) ግምገማ

ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የክፍል ስራ፣ የቡድን ሥራ በመስጠት ወይም ቡድንን በማደራጀት የታማኝነት መርሆች የተላበሱ ሰዎች ባሕርያት ላይ እንዲወያዩ በማደረግ በምላሾቻቸው ላይ በመመስረት የተማሪን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ። በተጨማሪም ምሳሌዎችን እየጠቀሱ እንዲወያዩ በማድረግ መገምገም ይችላሉ።

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

ተግባር 1.5

1) አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባው የታማንነት መርሆች መገለጫ፡-
   - ህይወታቸውን የሚመሩት በእቅድ ነው፤
   - ማድረግ የፈለጉትን የሚያደርጉ ናቸዉ፤
   - በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑ መሰረታዊ መርሆችን የሚያከብሩ ናቸው፤
   - ውጫዊ ጫናዎችን የሚቋቋሙ እና አዎንታዊ አመለካከት ያላቸዉ ናቸዉ።
2) የታማኝነት ባህሪ ያላቸው ሰዎች፡-
   - የማያውቁትን እናውቃለን አይሉም፤
   - ሁሉንም ሰው በተመሳሳይ መንገድ ያስተናግዳሉ፤
   - በውጫዊ ግፊት ምክንያት መርሆዎቻቸውን አይተውም።
3) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሊያንጸባርቋቸው የሚገቡ የታማኝነት መርህ ፡-
   - ሁሉንም ተማሪ በእኩልነት ማየት፤
   - የተሰጣቸውን ሥራ በወቅቱ ማከናወን፤
   - እውነትን መናገር፤
   - ስነምግባር የጎደላቸውን ተማሪዎች መምከር።

## ትምህርት 1.5. የታማኝነት መርሆችን ባለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡

- ☞ የታማኝነት መርሆችን ባለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ይለያሉ፤
- ☞ የታማኝነት መርሆችን ባለመተግበር የሚመጡ ችግሮችን ይዘረዝራሉ፤
- ☞ የታማኝነት መርሆችን ባለመተግበር የሚመጡ ችግሮች ለመከላከል የድርሻቸውን ይወጣሉ፡፡

የትምህርቱ ይዘት

የታማኝነት መርሆች ባለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

🕐 ለዚህ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት 4

**አጠቃላይ ገለፃ**

በቀደሙ የትምህርት ይዘቶች የታማኝነት መርሆች ምንነት፣ የታማኝ ሰዎች ባህሪያት፣ የታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት እና መገለጫዎችን በዝርዝር ተብራርተዋል፡፡ ይህ ትምህርት ደግሞ የታማኝነት መርሆችን አለመተግበር እንደ ግለሰብ እና እንደ ማህበረሰብ ሊያመጣ የሚችላቸውን ችግሮችን ያቀርባል፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ➔ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

መምህር፣ በክፍል ውስጥ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎችን ማቅረብ
- ☞ አጭር ገለጻ ማድረግ
- ☞ ጥያቄ እና መልስ ማካሄድ
- ☞ የቡድን ውይይት

**ቅድመ ዝግጅት**

ለመማር ማስተማር ሂደት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችና ለተማሪዎች የሚረዱ ዋና ዋና ነጥቦችን ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱትን የማጣቀሻ መጽሃፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ አለቦት፡፡

## የመማር ማስተማር ሂደት

**1. መግቢያ**

- ☞ የታማኝነት መርሆችን አለመተግበር የሚያስከትሉ ችግሮችን ለተማሪዎቹ ያብራሩ፤
- ☞ የትምህርቱን የመማር ውጤቶች ለተማሪዎች ይግለፁ፣
- ☞ ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት እንዲረዱ የግንዛቤ ጥያቄ ማቅረብ አለብዎት፤
- ☞ የተማሪዎችን በጥልቀት የማሰብ ክህሎት የሚያዳብሩ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

- ☞ የታማኝነት መርሆች አለመተግበር የሚያስከትለው ችግሮችን በምሳሌ በማስደገፍ አጭር መግለጫ ለተማሪዎቹ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ይጀምሩ፡፡
- ☞ በተጨማሪም ከዚህ ርዕስ ጋር የሚዛመዱ ምሳሌዎችን በማንሳት ተማሪዎች እንዲወያዩባቸው ያድርጉ፡፡

**3. ማጠቃለያ**

- ☞ የታማኝነት መርሆች አለመተግበር የሚያስከትላቸው ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹን በመከለስ የእለቱን ትምህርት ማጠናቀቅ አለቦት፡፡

**4. ክትትል እና ግምገማ**

ሀ) ክትትል

- ☞ ተማሪዎች የታማኝነት መርሆች አለመተግበር የሚያስከትላቸውን ችግሮች እንዲረዱ በዋና ዋና ነጥቦች ላይ እንዲወያዩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን በመከታተል አዎንታዊ ግብረመልስ በመስጠት ማበርታታት አለቦት፡፡

ለ) ግምገማ

ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት መረዳታቸውን ለማረጋገጥ፣ የክፍል ስራ፣ የቡድን ሥራ በመስጠት ወይም ቡድንን በማደራጀት የታማኝነት መርሆች አለመተግበር የሚያስከትላቸውን ችግሮች ላይ እንዲወያዩ በማደረግ በምላሾቻቸው ላይ በመመስረት የተማሪን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ፡፡

- ☞ በተጨማሪም ምሳሌዎችን እየጠቀሱ እንዲወያዩ በማድረግ መገምገም ይችላሉ፡፡

## የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 1.6

1. የታማኝነት መርሆች አለመተግበር የሚያስከትላቸው ችግሮች፡-
   - በራስ መተማመንን ይቀንሳል፤
   - በሰዎች መካከል መተማመንን ያጠፋል፤
   - መልካም ግንኙነትን ያበላሻል፡፡
2. በትምህርት ቤት ውስጥ የታማኝነት መርሆች አለመተግበር የሚያስከትላቸው ችግሮች፡-
   - ፈተና መኮረጅ፣
   - ትምህርት በትክክል አለመከተል፤
   - በመምህራን የሚሰጡ ስራዎችን አለመስራት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ

መመሪያ አንድ፡ እውነት/ሐሰት

1) ሐሰት
2) ሐሰት
3) እውነት
4) ሐሰት

መመሪያ ሁለት: ምርጫ

1) ሐ
2) ሀ
3) መ
4) ሐ

መመሪያ ሶስት: አጭር መልስ

1. የታማኝነት ምንነት፡-
   - የግለሰቡን በጎነት እና እሴቶች በተግባር ላይ ማዋል ማለት ነው፡፡
   - የታማኝነት ዋና ዋና መርሆችንና እሴቶችን በተግባር ላይ ማዋል ነው፡፡
2. የታማኝነት መርህ የተላበሰ ሰው ባህሪያት፡-
   - ታማኝነት፣
   - እብሪተኛ አለመሆን፣

- ኃላፊነትን መውሰድ፣
- ቋሚ ባህሪ ማሳየት፤
- ቁርጠኝነት፤
- ለሌሎች የሚያስቡና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

3. የታማኝነት መርሆችን በመተግበር የሚገኘው ጥቅም፡-
   - ማህበራዊ ግንኙነቶችን ያጠናክራል፤
   - ማህበራዊ ልማትን ይጨምራል፤
   - ችግርን የመፍታት ችሎታን ያዳብራል፤
   - በሰዎች ዘንድ ታማኝነትን እና ክብርን ይሰጣል፡፡
4. በትምህርት ቤት ውስጥ ከተማሪዎች የሚጠበቁ የታማኝነት መርሆች ምሳሌዎች፡-
   - እውነትን መናገር፤
   - ስህተትን መቀበልና እና ወደ ስህተቱ አለመመለስ፤
   - ቃል ኪዳንን መጠበቅ፤
   - የትምህርት ቤቱን ንብረት መንከባከብ፤
   - ጥፋት ካዩ ዝም ብለው አለማለፍ ፡፡
5. የታማኝነት መርሆችን አለመተግበር የሚያስከትሉ ችግሮች፡-
   - በሰዎች መካከል አለመተማመንን መፍጠር፤
   - መልካም ጓደኝነትን ያሳጣል፡፡

# ምዕራፍ 2 ፡ ሕግን ማክበር

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የሕግ ትርጉም፣ህግ የማክበር ምንነትና ህግን አለማክበር የሚያስከትለው ችግር ላይ ያተኩራል፡፡ በዚሁ መሰረት የሕግ ምንነትን በማብራራት የሚጀምር ሲሆን በመቀጠልም የሕጎችን ትርጉምና አስፈላጊነት ያብራራል፡፡ ከዚያም ሕግ አክባሪ ሰው የሚያሳየውን ባህሪ ይዘረዝራል፡፡ በመጨረሻም ሕግን አለማክብር የሚያስከትለውን ችግር ያብራራል፡፡

## የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- ☞ ሕግ የማክበር ምንነት መግለጽ፤
- ☞ ሕግ የማክበር አስፈላጊነትን ማብራራት፤
- ☞ የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያትን መዘርዘር፤
- ☞ ህግን አለማክበር የሚያስከትለውን ችግር መግለጽ፡፡

ለምዕራፉ የተመደበው የክፍለ ጊዜ ብዛት ፡20

ትምህርት 1፡ ሕግ የማክበር ምንነት

ትምህርት 2፡ ሕግ የማክበር አስፈላጊነት

ትምህርት 3፡ የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያት

ትምህርት 4፡ ሕግን አለማክበር የሚያስከትለው ችግር

## ትምህርት 2.1፡ ሕግ የማክበር ምንነት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ  የመማር ብቃት፡-

በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፣

- ☞ ሕግ የማክበር ምንነት ያብራራሉ፡፡

**የተመደበው የክፍለ ጊዜ ብዛት፡-4**

የትምህርቱ ይዘቶች

1. ሕግ የማክበር ምንነት
2. የሕግ አላማ

**አጠቃላይ ገለፃ**

ይህ ክፍለ ትምህርት ስለ ሕግ፣የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያትና ስለ ሕግ አላማ አጭር መግቢያ በመስጠት ይጀምራል፡፡ በመቀጠል ሕግ አክባሪ ዜጋ ማለት ምን ማለት እንደሆነና ምን ምን

ባህሪያት እንደሚያካትት ያብራራል። ይህም ተማሪዎች ስለ ሕግ የተሻለ ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል።

**የመማር ማስተማር ሂደት**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ምስል ድምፅ ፎቶ/ሥዕል ወዘተ

ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

መምህር፣ በክፍል ውስጥ የሚከተሉትን የመማር-ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ። እነሱም

- የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- የዕለቱን ትምህርት ማስተዋወቅ
- ስለ ዕለቱ ትምህርት አጭር ማብራሪያ መስጠት
- ጥያቄና መልስ ማካሄድ ሊሆን ይችላል

**ቅድመ ዝግጅት**

- መምህር፣ በመጀመሪያ የመማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት ይጠበቅቦታል።
- እንዲሁም በዚህ ትምህርት ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ለይተው አጭር ማስታወሻ ማያዝ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ለርዕሱ አጋዥ የሆኑትን የተለያዩ መጽሃፎችን በማንበብ ይዘጋጁ።

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**1. መግቢያ**

የዕለቱን ክፍለ ትምህርት ለተማሪዎች አጭር መግቢያ ያቅርቡና ሕግ የሚለውን ቃል ትርጉሙን በማብራራት መጀመር ይችላሉ፤ ወይም የመማር ውጤቶችን መግለፅ ይቻላል። በመቀጠል የግንዛቤ ወይም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የዕለቱን ትምህርት መጀመር ይችላሉ።

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

ስለ ሕግ ትርጉምና የሕግ አክባሪ ሰዉ ባህሪ ምሳሌዎችን በመስጠት የዕለቱን ትምህርት በማብራራት ወይም በውይይት መጀመር ይችላሉ። በዚህ ሂደት ተማሪዎች ሕግ የማክበርን አስፈላጊነት እዲያብራሩ ያድርጉ። እንዲሁም የሕግን ትርጉምና ዓላማ፣ ለተማሪዎች በዝርዝር በማስረዳት የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ ይቻላል።

## 3. ማጠቃለያ

የትምህርቱን ዋና ዋና ፅንሰ ሀሳቦችን ለተማሪዎቹ በአጭሩ ያብራሩ። በመቀጠል ስለ ሕግ ትርጉም፣ የሕግ አክባሪ ሰዉ ባህሪና ስለሕግ ማክበር አስፈላጊነት በቂ ማብራሪያ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችለሉ።

## 4. ክትትል እና ግምገማ

ሀ) ክትትል

ተማሪዎች ትምህርቱን በደንብ እንዲረዱ ገንቢ ግብረመልስ መስጠት ያስፈልጋል። ይህም ስለ ሕግ ትርጉም፣ የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያትና ስለ ሕግ ጥቅሞች እንዲወያዩ በማድረግ የተማሪዎቹን ግንዛቤ መከታተል ይችላሉ፤ወይም የቡድን ስራ በመስጠት ክንውናቸውን መከታተል ተገቢ ነው። በተጨማሪም በውይይቱ መሣተፋቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዱን የቡድን አባል ሃሳቡን እንዲያንጸባርቅ በማድረግ የተማሪዎቹን ግንዛቤ መከታተል ይችላሉ።

ለ) ግምገማ

ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት መረዳታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ይህም የክፍል ስራዎችን በመስጠት ወይም የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሊከናወን ይችላል። ተማሪዎች በቡድን ሆነው የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን መገምገም ይችላሉ።

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 2.1**

1

- የዜጎችን መብትና ግዴታ ያሳውቃል
- የዜጎችን ስነ ምግባር ለመቅረፅ ይረዳል
- የዜጎችን እኩልነት ለማረጋገጥ ይጠቅማል

2.

- የሀገርን ሕግ ለማክበር መዘጋጀት
- የሀገርን ሕግ ማወቅና ማክበር
- አለመግባባትን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት መሞከር

3.

- ተማሪዎች ሕግንና የትምህርት ቤታቸውን ደንብ ማክበር አለባቸዉ፡፡
- ተማሪዎች በመምህሩ የተሰጣቸዉን ስራ ማጠናቀቅ አለባቸዉ
- ተማሪዎች ከጉደኞቻቸዉ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት መልካም እንዲሆን ማድረግ አለባቸው

ተግባር 2. 2

1. የሽያጭ ደረሰኝ አለመስጠት
2. ያለደረሰኝ ሽያጭ ማድረግ አልነበረበትም
3. ሕግን አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንም

**ትምህርት 2. 2. ሕግ የማክበር አስፈላጊነት**

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማርያ ብቃት፡-

- ሕግ የማክበር አስፈላጊነት ያብራራሉ፡፡

የትምህርቱ ይዘት

1. ሕግ የማክበር አስፈላጊነት

- የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-5

መግቢያ

መምህር፣ ሕግ ማክብር ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ተማሪዎችን በመጠየቅ ይጀምሩ፡፡ በመቀጠል ሕግን ማክበር እንደ ግለሰብ ወይም እንደ ማህበረሰብ ያለውን ጥቅም ተማሪዎች እዲወያዩ ማድረግ ያሰፈልጋል፤ በመጨረሻ ሕግ ማክብር ያለውን ጥቅሞች እንዲወያዩ በማበረታታት የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

የመማር ማስተማር ሂደት

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ፎቶ፣ ድምፅ፣ ምስል የመሳሰሉት

የተመረጡ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር ፣የሚከተሉትን የመማር-ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላል፡፡

- የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- የዕለቱን ትምህርት ማስተዋወቅ

- ስለዕለቱ ትምህርት አጭር ማብራሪያ መስጠት
- ጥያቄና መልስ ማካሄድ ሊሆን ይችላል።

**ቅድመ ዝግጅት**

- በመጀመሪያ የመማሪያ ወይም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በመቀጠል ከርዕስ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን መጻሕፍትን በማንበብ መዘጋጀት ጠቃሚ ነው። በዚሁ መሰረት የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦችን በመለየት ተማሪዎች እንዲወያዩ ዝግጅት ማድረግ ጠቃሚ ነው።

የመማር ማስተማር ሂደት

**1. መግቢያ**

በመጀመሪያ ስለ ሕግ ማክበር አስፈላጊነት በማስረዳት ትምህርትዎን መጀመር ይችላሉ። በመቀጠል የትምህርቱን አላማ ተማሪዎቹ እንዲያውቁት ያድርጉ። ሕግ የማክበር አስፈላጊነትን በማብራራት ስለ ሕግ ማክበር አስፈላጊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የዕለቱ ትምህርት ይጀምሩ።

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

ስለ ሕግ ማክበር አስፈላጊነትና የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪ ምሳሌዎችን በመስጠት የዕለቱን ትምህርት በማብራራት ወይም በቡድን ውይይት መጀመር ይችላሉ። በመቀጠል ተማሪዎች ሕግ የማክበርን አስፈላጊነት እዲያብራሩ ያድርጉ። እንዲሁም የሕግ ምንነት፣ ዓላማ በዝርዝር ማስረዳት አስፈላጊ ነው።

**3. ማጠቃለያ**

የትምህርቱን ዋና ዋና ፅንሰ ሀሳቦች ለተማሪዎቹ በአጭሩ ያብራሩ። በመቀጠል፣ ስለ ሕግ፣ የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪና ስለሕግ ማክበር አስፈላጊነት ለተማሪዎች በቂ ማብራሪያ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችለሉ።

4. **ክትትል እና ግምገማ**

ሀ) ክትትል

ተማሪዎች ስለ ሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያትና ስለ ሕግ ማክበር ጥቅሞች እንዲወያዩ በማድረግ መከታተል ይችላሉ። እንዲሁም ተማሪዎች ትምህርቱን በደንብ እንዲረዱ የቡድን ስራ በመስጠት ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ ማድርግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ተማሪዎቹ በውይይቱ መሣተፋቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዱን የቡድን አባል ያለዉን ግንዛቤ እንዲያንጸባርቅ በማድረግ መከታተል ይችላሉ።

ለ) ግምገማ

ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት መረዳታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ይህም የክፍል ስራዎችን በመስጠት ወይም የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሊከናወን ይቻላል።ተማሪዎችን በቡድን ሆነው ሕግ አክባሪ ሰው በሚያሳየው ባህሪ ላይ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን መገምገም ይችላሉ።

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

ተግባር 2. 3

1)

- ነፃነትን ለማግኘትና ለመደሰት
- ሰላምን ለማግኘት
- ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ለማስፈን
- ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ
- የራስንና የዜጎችን ጥቅም ለማስጠበቅ።

2)

- ድርጊታችን የሌሎችን መብት የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን።
- የሀገራቸውን ህግ ማወቅና ማክብር
- የራስንና የሀገርን ደህንነት ማረጋገጥና አጠራጣሪ እንቅስቃሴዎች ሲገጥም ለመንግስት ማሳወቅ።

3)

- ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን ሕጎችና ደንቦች ማወቅና ለሕግ መታዘዝ አለባቸው።
- ከእኩዮቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት ማድረግ
- የሌሎች ተማሪዎችን ንብረት እንደራሳቸው ንብረት መንከባከብ
- የትምህርት ቤት ንብረቶች ያለአግባብ እንዳይጠፋ ወይም እንዳይበላሽ ጥንቃቄ ማድረግና የመሳሰሉት ናቸው።

## ትምህርት 2.3፡ የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማርያ ብቃቶች፡-

- የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያትን ይለያሉ፤
- የሕግ አክባሪ ሰዉ ባህሪ ምሳሌዎችን ይሰጣሉ።

**የትምህርቱ ይዘቶች**

- ☞ የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያት
- ☞ ሕግ አክባሪ ሰው መገለጫ ባህሪያት ምሳሌዎች ይሰጣሉ

🕐 **የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-5**

**አጠቃላይ ገለፃ**

በቀደሙት ክፍለ ትምህርት ስለ ሕግ ምንነት በተመለከተ ግንዛቤ ተፈጥሯል። በዚህ ክፍለ ትምህርት፣ተማሪዎች ከእውነተኛ ህግ አክባሪ ዜጎች ምን እንደሚጠበቅባቸው ይማራሉ። በዚህም ሕግ አክባሪ ዜጋ ምን ማወቅ እንዳለበትና በህብረተሰብ ውስጥ እራሱን እንዴት መምራት እንዳለበት ይገነዘባሉ።

**የመማር ማስተማር ሂደት**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ምስል፣ድምፅ ፎቶ ወዘተ

- ✍ የተመረጡ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር፣ በክፍል ውስጥ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ። ለምሳሌ

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ☞ የዕለቱ ትምህርት ማስተዋወቅ
- ☞ ስለ ዕለቱ ትምህርት አጭር ማብራሪያ መስጠት
- ☞ ጥያቄና መልስ ማካሄድ ሊሆን ይችላል

**ቅድመ ዝግጅት**

- ✍ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት።
- ✍ ለዚህ ርዕስ ቅርብ የሆኑ የተለያዩ መጽሃፎችን ማንበብና መዘጋጀት። እንዲሁም ዋና ዋና ነጥቦቹን ለይቶ ማስታወሻ መያዝ ያስፈልጋል።

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**1. መግቢያ**

መምህር ተማሪዎች የህግ አክባሪን ሰው ባህሪያት እንዲገልጹ በማበረታታት ወይም የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች በማብራራት የዕለቱን ትምህርት መጀመር ይቻላሉ። እንዲሁም ተማሪዎች ስለ ሕግ አከባሪ ሰው ባህሪ እንዲያስቡበት በቂ ጊዜ ይስጧቸው፣

ወይንም ስለ ሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያት ግንዛቤያቸውን እንዲዳብር የሚያነቃቁ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መጀመር ይችላሉ፡፡

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

ተማሪዎችን ስለ ሕግ አከባሪ ሰዉ ባህሪ የግንዛቤ ጥያቄ በመጠየቅ መጀመር ይቻላል፡፡ በመቀጠል፣ ስለ ሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያት በበለጠ እንዲዘረዝሩና እንዲወያዩበት ጊዜ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ማጠናከር ይችላሉ፡፡

**3. ማጠቃለያ**

የትምህርቱን ዋና ዋና ፅንሰ ሀሳቦች በአጭሩ ያብራሩ፡፡ በመቀጠል የእለቱን ትምህርቱ በመከለስ የሕግ አክባሪ ሰው ባህሪያት ምሳሌዎችን በመስጠት ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

**4. ክትትል እና ግምገማ**

ሀ) ክትትል

ተማሪዎች ስለ ሕግ አከባሪ ሰው ባህሪያትና ስለ ሕግ ማክበር ጥቅሞች ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ያድርጉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ትምህርቱን በደንብ እንዲረዱና ግብረመልስ እንዲሰጡ የቡድን ስራ ይስጧቸው፡፡ በተጨማሪም፣ በውይይቱ መሣተፋቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዱን የቡድን አባል ሃሳቡን እንዲያቀርቡ በማድረግ መከታተል ይችላሉ፡፡

ለ) ግምገማ

ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት መረዳታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም የክፍል ስራዎችን በመስጠት ወይም የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሊከናወን ይችላል፡፡ ተማሪዎችን በቡድን ሆነው ስለ ሕግ አክባሪ ሰው ባህሪ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ በማደርግ መገምገም ይቻላል፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

ተግባር 2.4

1)

- ሕግ የሕዝብ ፍላጎት መገለጫ መሆኑን ማወቅ፡፡
- ሕግን ለማክበር ዝግጁ መሆን፡፡

2)

- ሕግ አክባሪ ዜጋ የሀገሪቱን ሕግጋት ሁል ጊዜ ማክበር አስፈላጊ መሆኑን ይገነዘባል፡፡
- በህብረተሰቡ ውስጥ ሕግና ስርዓት እንዲሰፍን የራስን ሃላፊነት መወጣት

- ሕግ አክባሪ ዜጎች ህግ ማህበራዊ ለውጥ መሆኑን ይገነዘባሉ።

3)

- ሕግ አክባሪ ዜጎች የሌሎችን መብት ከመጣስ ሊቆጠቡ ይገባል።
- ሕግ አክባሪ ዜጎችም ከሌብነትና ውሸት ድርጊቶች ሊታቀቡ ይገባል። በማህበረሰቡ ውስጥ በሰላም አብሮ መኖር ላይ ገንቢ ሚና አላቸዉ።

## ትምህርት 2.4. ሕግ አለማክበር የሚያስከትላቸው ችግሮች

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- ሕግ አለማክበር የሚያስከትለውን ችግር ይለያሉ፤
- ሕግ አለማክበር ያለውን ችግር በምሳሌ ያብራራሉ።

**የትምህርት ይዘት**

1) ሕግ አለማክበር የሚያስከትለው ችግር

• የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-6

አጠቃላይ ገለፃ

በኅብረተሰቡ ውስጥ የሥርዓት አልበኝነት መስፋፋት ጎጂ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህም የግለሰብንና የህብረተሰቡን አጠቃላይ ህይወት ያቃውሳል። ከዚህ አንፃር ለተማሪዎች ሕግን አለማክበር የሚያስከትለውን ችግር በደንብ ሊያስረዱ የሚችሉ ተዛማጅ ምሳሌዎችን በመጥቀስ ማብራራት ያስፈልጋል።

የመማር ማስተማር ሂደት

የትምህርት መርጃ መሳርያዎች

- የተለያዩ ፎቶዎች / ምስሎች ወዘተ

ለመማር ለማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

መምህር፣ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላል። እነሱም፡-

- የግንዛቤ ጥያቄዎች መጠየቅ
- የዕለቱን ትምህርት ማስተዋወቅ
- ስለ ዕለቱ ትምህርት  ማብራሪያ መስጠት
- ጥያቄና መልስ ማካሄድ ሊሆን ይችላል።

**ቅድመ ዝግጅት**

- የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት።

- የዚህን ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦችን መያዝና ተጨማሪ መጽሃፎችን ማንበብና በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ተማሪዎች ሊወያዩባቸው ይገባል የምትሏቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ለይተዉ ማደራጀት ይገባል፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**1. መግቢያ**

ተማሪዎች ሕግን አለማክበር የሚያስከትለውን ችግር እንዲገነዘቡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የእለቱን ትምህርት መጀመር ይችላሉ፡፡ በመቀጠል የዕለቱን የትምህርት አላማ ለተማሪዎቹ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም, ተማሪዎች የተጠየቁትን እንዲመልሱ በቂ ጊዜ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

ሕግ አለማክበር የሚያስከትለውን ችግር በተመለከተ ዋና ዋና ሃሳቦችን ለተማሪዎቹ ካስረዱ በኋላ ተማሪዎቹ በዚህ ይዘት ላይ ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ የዕለቱን ትምህርት በስፋት ማብራራት ይችላሉ፡፡

**3. ማጠቃለያ**

ለተማሪዎች ሕግን አለማክበር የሚያስከትለዉን ችግር አጠቃላይ ሃሳብ በመስጠት የእለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

**4. ክትትል እና ግምገማ**

ሀ) ክትትል

ሕግን አለማክበር ሊያስከትል የሚያስከትለውን ችግር ከተማሪዎች ጋር መወያየትና ግንዛቤያቸውን መከታተል ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ትምህርቱን እንዲረዱ የቡድን ስራ በመስጠት የተማሪዎችን ግንዛቤ መከታተል ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በቡድን ውይይቶች ወቅት እያንዳንዱ አባል በውይይቱ ላይ መሳተፉን ማረጋገጥ አለቦት፡፡

ሀ) ግምገማ

የተማሪዎትን ግንዛቤ ለመገምገም የክፍል ስራ በመስጠት፣ ከእኩዮቻቸው ጋር እንዲወያዩ በማድረግ፣ የቤት ስራ ወይም የክፍል ስራ በመስጠት የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ፡፡

## የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 2.5

1.

- የደህንነት/ሰላም እጦት፤
- የሰብአዊ መብት መጣስ፤
- ሙስና፤
- አድሎአዊ አሰራር፤
- የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ፤
- ሕገወጥ የሕጻናት ዝውውር፤
- የግብር ስወራ፤
- የነፃነት እጦት፤
- የፍትህ መጓደል፤

2.

- የስምምነት ማጣት
- የዘፈቀደ አስተዳደር
- ሰላምና መረጋጋት መታጣት

3.

- ሕግ ማክበርና ማስከበር
- መጥፎ ዲርጊት ሲያጋጥማቸው ለመንግስት መጠቆም
- የሌሎች ሰዎችን መብት  ማክብር
- የራስን ሃላፊነት መወጣት

**ተግባር 2.6**

1.

- ሰዎች ክፋት ቢሰሩ መልስው በራሳቸው ላይ የሚደርስ መሆኑን
- ሰዎች የዘሩትን ያጭዳሉ የሚባለውም ለዚህ ጥሩ  ምሳሌ ይሆናል።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ

መመሪያ አንድ፡ እውነት/ሐሰት

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. እውነት

መመሪያ ሁለት፡ የምርጫ ጥያቄዎች መልስ

1. ለ
2. ሐ

3. ሐ 4. ሀ

መመሪያ ሶስት፡

1)

- ሕግ አክባሪ ማለት አንድ ሰው የሀገሪቱን ሕግ ለማክበር ፈቃደኛና ቁርጠኛ የሆነ ማለት ነው፡፡
- የህዝብን ፍላጎት ማክበር ማለት ነው፡፡
- ሁሉንም ተግባራት ከሀገራዊ ህግ ጋር መጣጣም አለበት፡፡

2)

- የራስንና የዜጎችን ጥቅም የሚያረጋግጡ ሕጎች እንዳሉ ያዉቃሉ፡፡
- ሕግ አክባሪ ዜጎች የህዝብን ሰላም ለማረጋገጥ የራሳቸዉን ሚና ይወጣሉ፡፡

3)

- ነፃነት በማግኘት መደሰት፡፡
- የሰላምን መጠበቅ፡፡
- ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል መኖር፡፡
- የሉዓላዊነትን ማረጋገጥ፡፡
- የራስንና የዜጎች ጥቅም መጠበቅ፡፡

4)

- አለመተማመን
- የሰብአዊ መብት ጥሰት
- ሙስና
- በአደንዛዥ ዕፅ ሱስ መያዝ
- የህፃናት ሕገወጥ ዝውውር
- የግብር ስወራ
- የነጻነት እጦት

# ምዕራፍ 3፡ መልካም ስነምግባር

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የመልካም ስነምግባርን ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ መልካም ስነ ምግባር ያለው ሰው ባህሪያት፣ የመልካም ስነምግባር መገለጫዎች እንዲሁም መልካም ስነምግባርን አለመተግበር የሚያስከትለውን ችግር ይዘረዝራል፡፡

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች**

- ☞ የመልካም ስነምግባር ምንነትን መግለጽ፤
- ☞ መልካም ስነምግባር ያለው ሰው የሚያሳየውን ባህሪይ መዘርዘር፤
- ☞ ለመልካም ስነምግባር አስፈላጊነት ትልቅ ቦታ መስጠት፤
- ☞ የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶችን በተግባር ማሳየት፤
- ☞ መልካም ስነምግባር አለመኖር የሚያስከትለውን ችግር መግለጽ፡፡

🕐 **ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት፡20**

**የምዕራፉ ይዛቶች፡-**

ትምህርት 1፡ የመልካም ስነምግባር ምንነት፤

ትምህርት 2፡ መልካም ስነምግባር ያለው ሰው ባህሪያት፤

ትምህርት 3፡ የመልካም ሥነ ምግባር አስፈላጊነት፤

ትምህርት 4፡ የመልካም ስነ ምግባር መገለጫ መንገዶች፤

ትምህርት 5፡ የመልካም ስነምግባር መጓደል የሚያስከትለው ችግር ፡፡

## ትምህርት 3.1. የመልካም ስነምግባር ምንነት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- ☞ የመልካም ስነምግባር ምንነት ይገልጻሉ፤
- ☞ የመልካም ስነምግባር ምሳሌዎችን ይዘረዝራሉ፤
- ☞ መልካም ስነምግባርን በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ውስጥ ይተገብራሉ፡፡

## የትምህርቱ ይዘት

1) የመልካም ስነምግባር ምንነት

ለዚህ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 2

**አጠቃላይ ገለፃ**

መልካም ስነ ምግባር ታማኝነትን፣ ርህሩህነትን፣ ለጋስነትን፣ ደግነትን እና የሌሎችን ስሜት መጋራት፣ እንዲሁም ሰዎች ለተሻለ ህይወት በመከባበር በጓደኝነት አብረው እንዲኖሩ መከባበርን ያካትታል፡፡ መልካም ባህሪ ያለው ሰው ለራሱ እንዲሆንለት የሚፈልገውን ሁሉ ሌሎችም እንዲኖራቸው ይመኛል፡፡

የልጆች ባህሪ በቤተሰብ፣ በጓደኞች እና በአካባቢው ማህበረሰብ ልምዶች ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ለምናሳያቸው ባህሪ እና ተግባራት ጥንቃቄ ማድርግ አለብን ፡፡ ምክንያቱም የሕጻናት አእምሮ ሁል ጊዜ ለነሱ ቅርብ ከሆኑ ሰዎች የሚያዩትን ድሪጊት እና የሚሰሙትን ስለሚቀብሉ ነው፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

➔ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል ወዘተ

☞ **ለመማር ማስተማር ዘዴዎች**

መምህር፣ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎች ይጠቀሙ፤

- የግንዛቤ ጥያቄዎች መጠየቅ
- ስለ ትምህርቱ በቂ ማብራሪያ መስጠት
- ጥያቄና መልስ ማካሄድ
- የቡድን ውይይት ማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡

**የቅድመ ዝግጅት**

በመጀመሪያ ለመማር ማስተማር ሂደት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ያዘገጁ፡፡ በመቀጠል ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የማጣቀሻ መጻሕፍት በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ አለቦት፡፡ በዚሁ መሰረት የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች——በመለየት ተማሪዎች እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

1. **መግቢያ**

   ስለ መልካም ስነምግባር ምንነት ለተማሪዎች ግልጽ የሆነ መግቢያ ይስጡ፤ ወይንም የትምህርቱን የመማር ውጤት ተማሪዎቹ እንዲያውቁ ያድርጉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በመጽሐፉ ውስጥ ላሉት የግንዛቤ ጥያቄዎች የራሳቸውን መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

## 2. የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር፣ ስለ መልካም ስነምግባር ምንነት መግለጫ ይስጡ፡፡ አያይዘውም መልካም ባህሪ የተላበሱ ተማሪዎች የሚያሳዩትን ምሳሌ በመጥቀስ መግለጽ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም መልካም ስነምግባርን በተግባር ማሳየት የሚቻልባቸውን መንገዶች በስፋት ይግለጹላቸው፡፡

ለምሳሌ፦

- ☞ መልካም ባህሪ የሚለው ቃል ያለውን ፍቺ፤
- ☞ የመልካም ስነምግባር ምንነት፤
- ☞ የመልካም ባህሪ መሰረታዊ መርሆች፤
- ☞ የመልካም ወይም የእኩይ ባህሪ መገለጫዎችና የመሳሰሉትን መጠቀም ይችላሉ፡፡

## 3. ማጠቃለያ

የመልካም ባህሪ ምንነትን አስመልክቶ አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማስታውስ የእለቱን ትምህርት ተጨባጭ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

## 4. ክትትል እና ግምገማ

### ሀ) ክትትል

ስለ መልካም ባህሪ የተለያዩ ነጥቦችን በማንሳት ተማሪዎች እንዲወያዩባቸው ያበረታቷቸው፡፡ በቡድን ወይም በተናጠል የቤት ስራ እንዲሰሩ በማድረግ ይከታተሉ፡፡ እንዲሁም ስለመልካም ባህሪ የመወያያ ርእስ በመስጠት የእያንዳንዱን ተሳትፎ በመከታተል አስፈላጊውን አዎንታዊ ግብረመልስ በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡

### ለ) ግምገማ

ፈተና ወይም የክፍል ስራ በመስጠት የተማሪዎችን የትምህርት ግንዛቤ ይገምግሙ፡፡ በተጨማሪም እንደ አስፈላጊነቱ ተማሪዎች በቡድን ከፋፍለው ስለ መልካም ባህሪያት ምንነት እንዲወያዩ በማድረግ በውይይታቸው ላይ በመመስረት መገምገምና ማበረታታት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የራሳቸውን የመልካም ባህሪይ መገለጫ ምሳሌዎች እንዲያቀርቡ በማድረግ ስለርእሰ ጉዳዩ ግንዛቤ መጨበጣቸውን ይገምግሙ፡፡

## የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 3.1

1. መልካም ስነምግባር በዕለት ከዕለት ህይወታችን ለሌሎች ደስታንና ምቾትን የሚሰጥ ተግባር ነው፡፡

2. የመልካም ባህሪይ መነሻ ዋና መለያው ታማኝነት እና የማህበረሰብ የአስተሳሰብ ልማዶች ውጤት ነው፡፡
   - ☞ መልካም ስነምግባር አለው የሚባል ሰው ታላቅን፣ ቤተሰብን፣ አረጋውያንን፣ መምህራንን፣ እናቶችን እና አባቶችን የሚያከብርና የተቸገሩትን የሚረዳ ነው፡፡
3. ትውልዱን በመልካም ስነምግባር ለመቅረፅ ነው፡፡
4. በራስ መተማመን፣ ጨዋ መሆን፣ ጥሩ ጓደኛ መምረጥ፣ ጠንክሮ መስራት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ትምህርት 3.2. የመልካም ሰው ባህሪ መገላጫዎች

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የማር ብቃቶች፡-

- ☞ የመልካም ሰው መግለጫ ባህሪያትን ይዘርዝራሉ፤
- ☞ መልካም ባህሪ ላላቸው ሰዎች ዋጋ ይሰጣሉ፤
- ☞ መልካም ባህሪ ያላቸውን ሰዎች ልምድ ይተገብራሉ፡፡

**የትምህርቱ ይዘት**

1) መልካም ባህሪ ያለው ሰው መገለጫዎች

🕐 ለዚህ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 6

**አጠቃላይ ገለፃ**

ተማሪዎች የዚህን የትምህርት ይዘት እንዲገነዘቡ ለመርዳት እያንዳንዱን ጽንሰሃሳብ ለተማሪዎቹ ማስተዋወቅ እና ይዘቱን ግልጽ በማድረግ ተዛማጅ ምስሎችን እና ምሳሌዎችን በመጠቀም ሊደግፏቸው ይገባል፡፡

መልካም ባህሪ ያለው ሰው የሚባለው በሕብረተሰቡ ውስጥ ጥሩ ስነምግባር የሚያሳይና ተቀባይነት ያለው ሰው ማለት እንደሆነ ማስረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸንን ለማስረዳት የመልካም ሰውን መሰረታዊ ባህሪ መገለጫዎች ማስተዋወቅ ይጠበቃል፡፡ በዚህ ትምህርት ተማሪዎች የመልካም ሰው መገለጫ ባህሪያትን ይማራሉ፡፡ እነሱም፡-

- ☞ ሀቀኝነት፤
- ☞ ለሌላው ደህንነት መጨነቅ፤
- ☞ ተጠያቂነት፤
- ☞ ለሌሎች ክብርና አድናቆት መስጠት፤
- ☞ ራስን መግዛት /መቆጣጠር፤

- ☞ ታማኝነት፤
- ☞ ምስጢር ጠባቂነት  እና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

➔ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ **ለመማር ማስተማር የተመረጡ  ዘዴዎች**

መምህር፣ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤
- ☞ አጫጭር ገለጻዎች መስጠት፤
- ☞ ጥያቄ እና መልስ ማካሄድ፤
- ☞ እርስ በርስ እንዲማማር  የቡድን ውይይት እና የመሳሰሉትን መጠቀም ይችላሉ፡፡

**የቅድመ ዝግጅት**

ለመማር ማስተማር ሂደት መሳካት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ያዘገጁ፡፡ በትምህርቱ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ አጭር ማስታወሻ አለቦት፡፡ በተጨማሪም ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱ የማጣቀሻ መጽሃፎችን በማንበብ ይዘጋጁ፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

1. መግቢያ
   - ☞ ይህንን ትምህርት ለተማሪዎች አጭር ገለጻ በመስጠት  መጀመር ይችላሉ፡፡
   - ☞ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን ለተማሪዎችዎ ያሳውቁ፡፡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመስጠት ተማሪዎችዎ በራሳቸው እንዲመልሱ ያበረታቱ፡፡
2. የትምህርት አቀራረብ

   የመልካም ባህሪ መገለጫዎች ላይ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ትምህርትዎን ይጀምሩ፡፡ የመልካም ሰው ቁልፍ መገለጫዎችን ለተማሪዎችዎ ይግለጹ፡፡ የመልካም ሰው መገላጫዎች ከሆኑት ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

   - ✓ ታማነት፤
   - ✓ ሀቀኝነት፤
   - ✓ ለሌሎች ሰዎች ክብር መስጠት፤
   - ✓ ተጠያቂነት፤

✓ እራስን መቆጣጠር ከሚጠቀሱት ውስጥ ናቸው፡፡

## 3. ማጠቃለያ

የዕለቱን የትምህርት ይዘት የመልካም ባህሪ መገለጫዎችን አስመልክቶ አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማሰታወስ ትምህርቱን ተጨባጭ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ፡-

- መሰረታዊ የመልካም ሰው መገለጫ ባህሪያት ማብራራት፤
- መልካም ስነ ምግባር ያለው ሰው ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 4. ክትትል እና ግምገማ

### ሀ) ክትትል

የመልካም ባህሪ አስፈላጊነትን በተመለከተ ቁልፍ ነጥቦችን ለተማሪዎች መነሻ ሀሳብ በመስጠት የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡ የእለቱን ትምህርት እንዲረዱ የተለያዩ የቡድን ተግባሮችን በመስጠት እንዲማማሩ ማድረግ ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱን ቡድን የመልካም ባህሪያ መገለጫዎችን እንዲያብራሩ ያድርጉ፡፡ ተሳትፏቸውንም በመከታተል ገንቢ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ በመጨረሻም የመልካም ሰው ባህሪያት ላይ ተማሪዎች የሰጡትን በማቀናጀት ሀሳብ በመስጠት ትምህርቱን ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

### ለ) ግምገማ

ተማሪዎች ስለትምህርቱ ግንዛቤ ማዳበራቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ወይም የክፍል ስራዎችን በመስጠት መገምገም ይችላሉ፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ እና የቡድን አባላትን ሃሳብ ሲለዋወጡ በመመልከት ግምገማ ማድረግ ይችላሉ፡፡

### የተግባር ጥያቄዎች መልስ

### ተግባር 3.2

1) የመልካም ሰው መገለጫ ባህሪያት የሚባሉት፡-
   - ሀቀኝነት፤
   - ራስን መቆጣጠር፤
   - ተጠያቂነት፤
   - ታማኝነት፤
   - ፍትሃዊነት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
2. መ/ር/ት፡- ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ መተግበር ያለባቸውን መልካም ባህሪያት ግለፁላቸው፡፡

**ተግባር 3.3**

- ታማኝ ሰው ሁል ጊዜ እውነት የሚናገር፣ የሚሰራ እና ስርቆሽ ውስጥ የማይሳተፍ ነው።

**ተግባር** 3.4

1. ቤተሰብን ማክብር በሕብረተሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው። ምክንያቱም የሕብረተሰቡን እሴት ማክበር ደስታን ይሰጣል፤ መተማመንን ይፈጥራል፤ የእርስ በእርስ ግኑኙነትን ያጠናክራል፤ በኑሮ ውስጥ ጭንቀትን ይቀንሳል፤የአእምሮ መረጋጋትን ይሰጣል፤ እንዲሁም ቅን አመለካከት እንዲኖረን ያደርጋል ።
2. ቤተሰብን አለማክበር የሚያስከትለው ችግር፤

መምህር ለጥያቄ ተራ ቁጥር 2 እና 3 ተማሪዎች በጉዳዩ ላይ እንዲወያዩ ያበረታቷቸው። ከዚያም መልሱን ከእራስዎ ልምድና ከአነበቡት መፅሐፍ ላይ በመመረኮዝ ሀሳብ ይስጧቸው።

## ትምህርት 3.3. የመልካም ስነምግባር አስፈላጊነት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- ስለ መልካም ስነምግባር አስፈላጊነት ይገልጻሉ፤
- ለመልካም ስነምግባር አስፈላጊነት ትኩረት ይሰጣሉ።

**የትምህርቱ ይዘት**

**1) የመልካም ስነምግባር አስፈላጊነት**

**ለዚህ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት: 3**

**አጠቃላይ ገለፃ**

በዚህ ትምህርት የመልካም ስነምግባር አስፈላጊነትን ይማራሉ። መልካም ስነምግባር በጓደኝነት፣ በትምህርት ቤት እና በአጠቃላይ በህብረተሰብ ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት ለተማሪዎቹ ማስረዳት አለቦት። ተማሪዎች ስለመልካም ስነምግባር መማራቸው በማኅበራዊና በግል ሕይወታቸው ጥሩ ፀባይ እንዲያሳዩ ይረዳቸዋል። መልካም ስነምግባር በማሳየታቸው በህብረተሰቡ ዘንድ ክብር እና እምነት እንዲጎናጸፉ ይረዳቸዋል። ከሁሉም በላይ፣ መልካም ስነምግባር በቤተሰብ ውስጥ፣ ትምህርት ቤት ካሉ ጓደኞች እና ከመሳሰሉት ጋር ለሚፈጠር ግንኙነት ትልቅ ጥቅም እንዳለው ማስረዳት ይጠበቅቦታል።

የመማር ማስተማር ዘዴ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

→ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

መምህር፣ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎች መጠየቅ፤
- ☞ የዕለቱን ትምህርት ማስተዋወቅ፤
- ☞ ስለ ዕለቱ ትምህርት ማብራሪያ መስጠት፤
- ☞ ጥያቄና መልስ ማካሄድንና የመሳሰሉትን ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

ለመማር ማስተማር ሂደት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ያቀነቀጁ፡፡ ለዚህ ትምህርት ይዘት የሚረዱ ዋና ዋና ነጥቦችን ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱ የማጣቀሻ መጽሃፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ አለቦት፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**1. መግቢያ**

ለዚህ ትምህርት አጭር መግቢያ ይስጡ፡፡ ለተማሪዎችዎ የትምህርቱን ዓላማ ይግለጹላቸው፤ ወይንም በዚህ መጽሓፍ ውስጥ ለቀረቡ ተግባራት የራሳቸውን መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡

**የትምህርቱ አቀራረብ**

መምህር፣ መልካም ስነ ምግባር ለቤተሰብ፣ ለትምህርት ቤት ጓደኞች ለጎረቤትና ለማህበረሰብ መልካም ግንኙነት አስፈላጊ እንደሆነ በመግለጽ ይጀምሩ፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ከዚህ በታች ያሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ማካተት ይጠበቅቦታል፡፡ እነሱም፡-

- ✓ በራስ መተማመን፤
- ✓ ለራስ ክብር መስጠት፤
- ✓ መደሰት፤
- ✓ መልካም ምሳሌ መሆን፤
- ✓ ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር፤
- ✓ ለሌሎች ክብር መስጠት፤
- ✓ መተባበር፣ አብሮ መስራት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**2. ማጠቃለያ**

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ነጥቦች በመከለስ ለተማሪዎች በቂ ገለጻ በመስጠት የእለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

**3. ክትትል እና ግምገማ**

**ሀ)ክትትል**

ተማሪዎች ሃሳብ እንዲለዋወጡ መከታተልና ግብረመልስ መስጠት ይገባዎታል፡፡ ተማሪዎች ይህን ትምህርት በደንብ እንዲረዱት የቤት ስራ በመስጠት አተገባበራቸውን ይከታተሉ፡፡ በመጨረሻም ስለመልካም ስነምግባር አስፈላጊነት የራሳቸውን ሃሳብ እንዲሰጡ በማድረግ ተማሪዎችን መከታተል አለቦት፡፡

**ለ) ግምገማ**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት መገንዘባቸውን ለማረጋገጥ፡ የክፍል፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ውይይት በመስጠት የእያንዳንዱን ተሳትፎ መገምገም ይችላሉ፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

ተግባር 3.5

1.

- ☞ በራስ መተማመን ያጎለብታል
- ☞ ለራስ ክብር ለመስጠት ይረዳል
- ☞ መልካም ምሳሌ ለመሆን ይጠቅማል
- ☞ መልካም ግንኙነትን ያመናክራል

2. አዎ፡፡ መ/ር/ት፡- ምክንያቱን አብራሩላቸው፡፡

## ትምህርት 3.4. የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶች

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- ☞ የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻሳደጊያ መንገዶችን ይገልጻሉ፤
- ☞ የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶችን ይለያሉ፡፡

## የትምህርቱ ይዘት

### 1) የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶች፤

ለዚህ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 7

**አጠቃላይ ገለፃ**

ይህ ትምህርት ተማሪዎች የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶችን የሚለዩበትና ምንነቱን የመብራራት አቅም የሚያዳብሩበት ነው፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ➔ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል
- ☞ ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

መምህር፣ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላል፡-

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎች መጠየቅ፤
- ☞ የዕለቱን ትምህርት ማስተዋወቅ፤
- ☞ ስለ ዕለቱ ትምህርት ማብራሪያ መስጠትና
- ☞ ጥያቄና መልስ ማካሄድ ሊሆኑ ይችላል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

ለመማር ማስተማር ሂደት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ያዘገጁ፡፡ በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ ለተማሪዎች የሚረዱ ዋና ዋና ነጥቦችን ያቀናጁ፡፡ በተጨማሪም ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱ የማጣቀሻ መጽሃፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ አለቦት፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**1. መግቢያ**

የእለቱን  ትምህርት ለተማሪዎች አጭር መግቢያ በመስጠት ይጀምሩ፡፡ ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶችን ለተማሪዎች ይግለጹ፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን በጥልቀት የማሰብ ችሎታ የሚያጠናክሩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መልስ እንድሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶችን እንዲለዩ የተለያዩ የመወያያ ነጥቦችን በመስጠት መጀመር ይችላሉ፡፡ የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶች ላይ በምሳሌ የተደገፈ በቂ ማብራሪያ በመስጠት ያስረዷቸው፡፡

3. ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት ውስጥ የተካተቱትን ዋና ዋና ነጥቦች በማንሳት ለተማሪዎች ግለጹላቸው፡፡ የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶች ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉትን በማቅረብ ትምህርቱን ያጠቃሉ፡፡

**4. ክትትልና ግምገማ**

**ሀ)ክትትል**

በመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶች ላይ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ እንዲሰጡ መከታተልና ግብረ መልስ መሰጠት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶች ሊሆኑ የሚችሉትን እንዲገነዘቡ የተለያዩ ተግባራትን በመስጠት ክትትል ያድርጉ፡፡

**ለ) ግምገማ**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት መገንዘባቸውን ለማረጋገጥ ጥያቄና መልስ ወይም የክፍል ስራ በመስጠት ብቃታቸውን ይመዝኑ፡፡ በተጨማሪም፣ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል በዋና ዋና ነጥቦች ላይ እንዲወያዩ በማድረግ ባነሷቸው ነጥቦች ላይ በመመረኮዝ ይገምግሟቸው፡፡

የተግባር ጥያቄዎች መልስ

**ተግባር 3.6**

1. አዎን ይቻላል፡፡
2. የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶች:-
   - ✓ ራስን መቆጣጠር (መግዛት)፤
   - ✓ የማህበረሰቡን እሴቶች መቀበልና መከተል፤
   - ✓ የትምህርት ቤትን ህግ ማክበርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ተግባር 3.7**

1. ራስን መቆጣጠር ማለት፣ ከአላስፈላጊ ስሜትና ድርጊት ራስን መጠበቅ ነው፡፡
2. መ/ር/ት:-የመልካም ስነምግባር መጎልበቻ መንገዶችን አብራሩላቸው፡፡

3. ራስን መቆጣጠር ወጣቶች ትክክለኛ ካልሆነ ባህሪይ እንዲቆጠቡ ያደርጋል፡፡

**ተግባር 3.8**

1. ሕግን ማክበር ማለት፣ እንደማህበረሰቡ እሴትና ሕግ መኖር ነው፡፡
2. ከጓደኞች ጋር መልካም ግንኙነት መመስረት፣በትምህርት ክፍል ጊዜ መገኘትና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡
3. ተማሪዎች ለሕግ ያላቸውን ታማኝነት የሚያሳዩባቸው መንገዶች የደንብ ልብስ በመልበስ፣ የቤት ስራ በመስራት፣የክፍልና የግል ንጽህናን በመጠበቅ፣በንቃት በመሳተፍን እና በመሳሰሉት ነው፡፡

**ተግባር 3.9**

1. እሴት በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን መልካም ስነምግባሮችን ማክበር ማለት ነው፡፡
2. በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉት መልካም እሴቶች ፡
   - ታላላቆችንና አዛውንቶችን ማክበር፤
   - የወላጆችን ትዕዛዝ መቀበል፤
   - የሰውን ልጅ በእኩልነት ማገልገል፤
   - እውነትን መናገር፤
   - እንግዶችን ማክበርና ማስተናገድ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ተግባር 3.10

1. መምህር፣ተማሪዎች የትምህርት ቤቶቻቸውን ህግና ደንብ እንዲገልጹ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡

## ትምህርት 3.5. በመልካም ስነምግባሮች መጓደል የሚከሰቱ ችግሮች

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎነጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃት፡-

- በመልካም ስነምግባሮች መጓደል የሚከሰቱ ችግሮችን ይገልጻሉ፡፡

**የትምህርቱ ይዘት**

1. በመልካም ስነምግባር መጓደል ሊከተሉ የሚችሉ ችግሮች

ለዚህ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 2

**አጠቃላይ ገለፃ**

ይህ ትምህርት በመልካም ስነምግባር መጓደል የሚከሰቱ ችግሮች ላይ ያተኩራል፡፡ መምህር፣ እያንዳንዱ ተማሪ በመልካም ስነምግባር መጓደል ሊከሰቱ በሚችሉ ችግሮች ላይ በክፍል ውስጥ እንዲወያዩበትና ልምድ እንዲለዋወጡበት ያበረታቷቸው፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ➔ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

**ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች**

መምህር፣ ከዚህ በታች ያሉትን ዘዴዎች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎች መጠየቅ፤
- ☞ ገለጻ መስጠት፤
- ☞ ጥያቄና መልስ ማካሄድ፤
- ☞ የቡድን ውይይትንና የመሳሰሉት ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

ለመማር ማስተማር ሂደት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ያቀናጁ፡፡ በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ ለተማሪዎች የሚረዱ ዋና ዋና ነጥቦችን አጭር ማስታወሻ ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱ የማጣቀሻ መጽሃፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**1. መግቢያ**

ይህን ትምህርት ለተማሪዎች አጭር መግቢያ በመስጠት ይጀምሩ፤በመቀጠል የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች ይግለጹ፡፡እንዲሁም የግንዛቤ ማጠናከሪያ ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

- ☞ በመልካም ስነምግባሮች መጓደል የሚከሰቱ ችግሮችና ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ለይተው በማንሳት በውይይት መልክ ይጀምሩ፤

**3. ማጠቃለያ**

- ☞ በመልካም ስነምግባሮች መጓደል ምክንያት ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮችን በተመለከተ ዋና ዋና ሃሳቦችን በመከለስ የእለቱን ትምህርት ማጠናነቅ ይችላሉ፡፡

**4. ክትትል እና ግምገማ**

**ሀ) ክትትል**

- ☞ በመልካም ስነምግባር መጓደል የሚከሰቱ ችግሮችን በተመለከተ ተማሪዎች የግል ሃሳባቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ያድርጉ፡፡ የሃሳብ አቀራረባቸውን ቅንጅትና በርእሱ ላይ ማተኮራቸውን ይከታተሉ፡፡
- ☞ ተማሪዎች ይህን ትምህርት በደንብ እንዲገነዘቡ ለማድረግ የቤት ስራ፣የቡድን ስራ፣ የክፍል ስራ በመስጠት መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት ይገባል፡፡
- ☞ በመጨረሻ በመልካም ስነምግባር መጓደል ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮችን ላይ ያላቸውን ሃሳብ እንዲገልጹ በማድረግ ክትትልዎን ያጠናክሩ፡፡

**ለ) ግምገማ**

- ☞ ተማሪዎች ይህን ትምህርት መገንዘባቸውን ለማረጋገጥ ጥያቄና መልስ በማካሄድ፣ የክፍል እና የቤት ስራ በመስጠት ይገምግሙ፡፡
- ☞ ተማሪዎች በቡድን ከተደራጁ በኋላ ዋና ዋና በሆኑ ነጥቦች ላይ እንዲወያዩ በማድረግ እያንዳንዱ የቡድን አባል በሚያደርገው ተሳትፎ ላይ ተመርኩዘው መገምገም ይችላሉ፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

ተግባር 3.11

1. በስነምግባር መጓደል ምክንያት ሊከሰቱ ከሚችሉ ችግሮች ውስጥ፡-

   ሀ) በተማሪዎች መካከል መከባበር መታጣት፤

   ለ) የትምህርት ቤትና የግል ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፤

   ሐ) የትምህርት ቤት ንብረት ማበላሸት፤

   መ) አርፍዶ ትምህር ቤት መሄድ፤

   ሠ) ከትምህርት ቤት መቅረት፤

   ረ) ስርቆት፤

   ሰ) የደንብ ልብስ አለመልበስ፤

   ሸ) መዋሸት፤

ቀ)መደባደብ እና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

**የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ**

**መመሪያ አንድ፡ እውነት/ሐሰት**

1) ሐሰት 3) ሐሰት 5) እውነት

2) እውነት 4) እውነት

**መመሪያ ሁለት ፡ የምርጫ ጥያቄዎች መልስ**

1) ሀ 2) መ 3) ሐ 4) መ 5) መ

**መመሪያ ሶስት፡ አጫጭር መልስ**

1)

| ተቁ | ቦታ | ራስን ማክበር | ሰዎችን ማክበር | አካባቢን ማክበር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ ክፍል | ✓ | | |
| 2 | ቤተ መጽሐፍ | | | ✓ |
| 3 | የትምህርት ቤት ግቢ | | | ✓ |
| 4 | ቤተሰብ | | ✓ | |
| 5 | ጎረቤት | | ✓ | |
| 6 | ማህበረሰብ | | ✓ | |

# ምዕራፍ 4፡ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኩራል፡፡ ይህም ስለ ማህበራዊ ግንኙነቶችና የተሻለ ኑሮ መኖርን የተመለከቱ ጉዳዮችን ያካትታል። በመሆኑም እንደ በጎ ፈቃድ አገልግሎት፣ የጋራ ተጠቃሚነት ያላቸው ተግባራት ላይ መሳተፍ፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ እና የመሳሰሉ ድርጊቶች በህብረተሰቡ ህይወት ላይ ስላላቸው ሚና በዝርዝር ቀርቧል። እንዲሁም ማህበራዊ እሴቶች የሚባሉት እንደ ባህላዊ ፍርድ ቤት፣ የበጎ አድራጎት(የዜግነት) አገልግሎት፣ ባህላዊ የመረዳዳት አደረጃጀት (ቡሳ ጎኖፋ) በምሳሌነት ቀርበዋል። በተጨማሪም እንደ ግብር፣ ቁጠባና የመሳሰሉት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቷቸዋል።

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- ☞ የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ምንነት መግለፅ፤
- ☞ የዜግነት (የበጎ ፈቃደኝነት) ተሳትፎ ያለውን ጠቀሜታ መገንዘብ፤
- ☞ በበጎ ፍቃደኝነት ስራ ውስጥ  መሳትፍ፤
- ☞ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ለህብረተሰቡ በጋራ መኖር ያላቸውን ሚና ማድነቅ፤
- ☞ የህብረተሰቡን ችግር ለመፍታት የቡሳ ጎኖፋ ተቋም የሚጫወተውን ሚና መረዳት፤
- ☞ ቁጠባ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ሚና ማብራራት፤
- ☞ ታማኝ ግብር ከፋዮች በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያላቸውን ሚና መዘርዘር፤

🕐 ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 20

ትምህርት 1: ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ምንነት

ትምህርት 2፡ የዜግነት (የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት) ውስጥ መሳተፍ

ትምህርት 3፡ ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደት (ባህላዊ ፍርድ ቤት)

ትምህርት 4፡ የመረዳጃ ማህበራት/ተቋማት ማጠናከር (ቡሳ-ጎኖፋ)

ትምህርት 5፡. የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን የሚያጠናክሩ ተቋማት (ቁጠባና ግብር)

## ትምህርት 4.1. የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ምንነት

ቢያንስ  ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- ☞ የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ምንነት ይገልጻሉ፤

☞ የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ አስፈላጊነትን ያደንቃሉ፡፡

**የትምህርቱ ይዘት**

1) የማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ምንነት

ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 5

**አጠቃላይ ገለፃ**

ይህ ትምህርት በማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኩራል፡፡ ማህበራዊ እንቅስቃሴ ማለት ህብረተሰቡ ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት የማህበረሰቡ አባላት በጋራ ሆነዉ የሚከውኑት ተግባር ነው፡፡ የእዚህ አይነቱ ተግባራት የማህበረሰቡን አባላት አንድ ላይ ስለሚያሰባስብ በማህበረሰቡ መካከል ጥሩ ግንኙነት ለመፍጠር ይረዳል፡፡ ይህም በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ችግር ለመፍታት በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ ሰዎች ስብስብ ሊከናወን ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፡- ገቢ፣ገንዘብ፣ንብረትወይም ማንኛውንም ኢኮኖሚያዊ ዓላማ ለማግኘት ሲባል የሚከናወን ተግባር ሊሆን ይችላል፡፡ ገቢን የሚያስገኝ፣ የኢንቨስትመንት ስራና ንብረት የሚያስገኝ ማንኛውም እንቅስቃሴ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይባላል፡፡ ስለዚህ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በግለሰቦች ወይም በህብረተሰብ ህይወት ዕድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ይኖረዋል፡፡ መምህር/ት ስለ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ምንነት የተለያዩ ምሳሌዎችን በማንሳት እንዲሁም ስለ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ለተማሪዎች ተገቢ ማብራሪያ ይስጡ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ➔ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ **ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች**

መምህር ፣የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄ መጠየቅ
- ☞ አጭር ገለጻ መስጠት
- ☞ ጥያቄ እና መልስ ማካሄድ
- ☞ የቡድን ውይይት ማድረግ

**ቅድመ ዝግጅት**

ለመማር ማስተማር ሂደት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ይምረጡ፡፡ በእዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ ለተማሪዎች የሚረዱ ዋና ዋና ነጥቦችን ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱትን የማጣቀሻ መጽሃፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ይኖርቦታል፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**2. መግቢያ**

መምህር፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ምንነት በመግለፅ እንዲሁም ማህበራዊ ኢኮኖሚካዊ እንቅስቃሴ በግለሰብ ወይም በህብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ያለውን ሚና ለተማሪዎች አጭር ማብራሪያ በመስጠት መጀመር ይችላሉ፡፡ በመግቢያው ላይ የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባትዎን አይርሱ፡፡

- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ምንነት፤
- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች አስፈላጊነት፤
- ስለ ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡

**3. የትምህርቱ አቀራረብ**

መምህር፣ ስለ ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ምንነት ለተማሪዎቹ ማብራሪያ በመስጠት የሚከተሉትን ነጥቦች እንዲገነዘቡ ያድርጉ፡፡

- የማህበራዊ እንቅስቃሴ ምንነት፤
- የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ምንነት፤
- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ትርጉም፤
- ለእያንዳንዳቸው እነዚህ ርዕሶች ምሳሌ በመስጠት ተማሪዎችን ያሳትፉ፡፡

**4. ማጠቃለያ**

በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የእለቱን ትምህርት ማጠናከርና ለተማሪዎቹ አጭር ማብራሪያ በመስጠት የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ በማድረግ የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ምንነት፤
- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጥቅም፡፡

## 5. ክትትልና ግምገማ

ሀ) ክትትል

ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በመከታተል የዕለቱን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡ ጥያቄ በመጠየቅ ያረጋግጡ ፡፡

ለ) ግምገማ

የክፍል ስራ፣የቤት ስራ የውይይት ጥያቄዎች በመስጠት ወይም የሙከራ ፈተና በመስጠት የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

ተግባር 4.1

1. ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት የማህበረሰብ አባላት በቡድን የሚሰሩት ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡.
2. የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በኑሮ ላይ ያላቸዉን ሚና፡-
   - ከተማሪ መጽሐፍ ወይም ከራስህ/ሽ መልስ በመስጠት ተማሪዎች እንዲወያዩና እንዲረዳዱ አበረታቷቸው፡፡

## ትምህርት 4.2. የዜግነት (የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት) ውስጥ መሳተፍ

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- የበጎ ፍቃደኝነት ተግባራትን ምንነትን ያብራራሉ፤
- የበጎ ፈቃደኝነት ተሳትፎን አስፈላጊነት ይዘረዝራሉ፡፡

የትምህርቱ ይዘት

1) በበጎ ፈቃድ ስራ ላይ መሳተፍ

ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት ፡4

**አጠቃላይ ገለፃ**

በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የዜግነት(የበጎ ፍቃደኝነት አገልግሎት) ማለት ከማህብራዊ አገልግሎት አንዱ ሲሆን ገንዘብን፣ ጊዜን፣ ጉልበትንና ዕውቀትን በራስ ፍላጎት ለማህበረሰብ አገልግሎት ማዋል ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ተግባር ገንዘብ ወይም ሽልማት ለማግኘት ሳይሆን ለህብረተሰቡ ጥቅም እና ክብር ሲባል የሚከወን ስራ ነው፡፡ ይህ ለሰዎች ክብር ሲባል ስራ በነፃ እና በግል ሙሉ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የሚከወን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የበጎ ፍቃደኝነት አገልግሎት ከሚባሉት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉትን ያካትታል፡፡ እነሱም፡-

የችግኝ ተከላ፣ለአቅመ ደካማዎች ቤት መስራት፣በማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

→ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ **ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች**

መምህር፣ የሚከተሉትን ዘዴዎች በመጠቀም ትምህርትዎን ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ እነሱም፡

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፤
- ☞ አጭር መግቢያ በመስጠት፤
- ☞ የትምህርቱን አላማ ለተማሪዎች በማብራራት፤
- ☞ ስለ ዕለቱ ትምህርት ጥያቄና መልስ በማድረግ፤
- ☞ የቡድን ውይይት በማካሄድ ሊሆን ይችላል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

መምህር/ት፣ ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት በቂ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅቦታል፡፡ ይህም የመማሪያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት፣ ለርዕሱ አጋዥ የሆኑ መጽሀፍትን ማንበብ ወይም የመማሪያ መጽሀፍን ከመምህሩ መምሪያ ጋር በማገናዘብ በቂ ዝግጀት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የመማር ማስተማር ሂደት

1) **መግቢያ**

መምህር፣ ስለ ዕለቱ ትምህርት አጭር ማብራሪያ መስጠት፤ ይህም የበጎ ፈቃድ አገልግሎትና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስፈላጊነትን በተመለከተ የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የዕለቱን ትምህርት መጀመር ይችላሉ፡፡

1) **የትምህርት አቀራረብ**

መምህር የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በተመለከተ ለተማሪዎች ማብራሪያ ይስጡ፡፡ በመቀጠልም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስፈላጊነትና በማህበረሰቡ ውስጥ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ያለውን ሚና ለተማሪዎች በቂ ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ለተማሪዎች በቂ ግንዛቤ ለመስጠት በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያለዉን የበጎ ፈቃደኝነት ምሳሌዎችን ለተማሪዎቹ ይግለፁ፡፡ ለምሳሌ፡

- ✍ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጥቅም፤
- ✍ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስፈላጊነት፤

- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለህብረተሰቡ የሚሰጠው ጥቅም፤
- የማህበረሰብ አገልግሎት ምሳሌዎችን መጥቀስ ይችላሉ።

2) ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ለምሳሌ እንደ

- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምንነት፤
- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስፈላጊነት፤
- የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ምሳሌዎችን ተማሪዎችን በማስታወስ የዕለቱን ትምህርት ማጠናቀቅ ይችላሉ።

3) ክትትል እና ግምገማ

ሀ) ክትትል

በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ መከታተል ወይም የቤት ስራቸውን እንዲሰሩ ማድረግ፤ እንዲሁም የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሳተፉ በማድረግ የተማሪዎቹን ግንዛቤ መከታተል ይችላሉ።

ለ) ግምገማ

መምህር፣ለተማሪዎች የተግባር ጥያቄዎችን በመስጠት ትምህርቱን መረዳታቸውን መገምገም ይችላሉ። ይህም የክፍልና የቤት ስራን በመስጠት ወይም የሙከራ ፈተና በመስጠት ተማሪዎችን መገምገም ያስፈልጋል።

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

ተግባር 4. 2

1. መምህር ተማሪዎች የእረፍት ጊዜያቸውን የት እንደሚያሳለፉ በመጠየቅ መልሳቸውን በማቀኛጀት ለክፍሉ ያብራሩ።
2. የእረፍት ጊዜ ጥቅም ገንዘብን ፣ጊዜን ጉልበትንና እውቀትን በራስ ፍላጎት ለማህበረሰብ አገልግሎት ለማዋልና ህብረተሰብን ለማገልገል ይጠቅማል፡፡

## ትምህርት 4.3. ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደት (ባህላዊ ፍርድ ቤት)

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- ባህላዊ ፍትህ ሂደትንና ዓላማን ይገልጻሉ።
- ባህላዊ ፍትህ አብሮ በመኖር ውስጥ ያለውን ሚና ያደንቃሉ።

**የትምህርት ይዘት**

1) ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደት

🕐 ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 4

**አጠቃላይ ገለፃ**

ይህ ርዕስ ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደትን ያብራራል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደትን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸዉ ግንዛቤ ይሰጣቸዋል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

➔ ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ **ለመማር ማስተማር የተመረጡ  ዘዴዎች**

መምህር፣ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡እነሱም፡-

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤
- ☞ የእለቱን ትምህርት ለተማሪዎች ማብራራት፤
- ☞ ስለ ዕለቱ ትምህርት አጭር ማብራሪያ መስጠት፤
- ☞ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤
- ☞ የቡድን ውይይቶችን ማካሄድ ሊሆን ይችላል፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር፣ ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ያዘጋጁ፡፡ እንዲሁም ከዚህ ትምህርት ይዘት ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን መጽሀፎችን በማንበብ ወይም የመማሪያ መጽሀፉን ከመምህሩ መምሪያ ጋር በማቀናጀት በቂ ዝግጅት ማድርግ ያስፈልጋል፡፡

የመማር ማስተማር ሂደት

**1. መግቢያ**

መምህር፣  ስለ ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደትአጭር መግቢያ ይስጡ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደት ለማህበረሰብ አገልግሎት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በማስረዳት ወይም የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የእለቱን ትምህርት መጀመር ይችላሉ፡፡

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

መጀመሪያ ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለተማሪዎችዎ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደት በህብረተሰብ አገልግሎት

ማዋል ያለውን ጠቀሜታ ለተማሪዎቹ ያስረዷቸው፡፡ ተማሪዎች በሚከተሉት ነጥቦች ላይ እንዲያተኩሩ አድርጉ፡-

- ☞ ባህላዊ ፍርድቤት ትርጉም
- ☞ የባህላዊ ፍርድ ቤት ተግባራት
- ☞ ባህላዊ ፍርድቤት ለህብረተሰቡ ያለው ጥቅም

**3. ማጠቃለያ**

መምህር፣ የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ለተማሪዎቹ በማብራራት የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ ፡፡ይህም፡-

☞ባህላዊ ፍርድቤት ትርጉም

የባህላዊ ፍርድ ቤት ተግባራት

☞ባህላዊ ፍርድቤት ለህብረተሰቡ ያለው ጥቅም ለተማሪዎች በማስረዳት የእለቱን ትምህርትን ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

4. ክትትል እና ግምገማ

ሀ) ክትትል

የዕለቱን ትምህርት በተመለከት በክፍል ውስጥ የተማሪዎች እንቅስቃሴ በመመልከት ወይም የቤት ስራ በመስጠት የተማሪዎቹን ተሳትፎ መከታተል ይችላሉ፡፡

ለ) ግምገማ

መምህር፣የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ ማረጋገጥ ይቻላሉ፡፡ ይህም የቤት፣ የክፍል ስራ በመስጠት ወይም ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩባቸው ጥያቄ በመስጠት እንዲሁም ተማሪዎች ከአቻዎቻቸው ጋር እንዲወያዩ በማድረግ ወይም ከራሳቸው ምሳሌ በመጥቀስ ሀሳብ እንዲለዋወጡ በማድረግ መገምገም ይችላሉ፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

ተግባር 4.3

1. በህብረተሰቡ ባህል መሰረት የህብረተሰቡን ባህላዊ እሴት ባከበረ መልኩ በመወያየት የሚከናወን ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ነው፡፡

ተግባር 4.4

1. በባህላዊ የፍርድ ቤት ሂደት ግን ጉዳዮች ሁሉ የሚታዩት የህብረተሰቡን ባህላዊ ዕሴት በጠበቀ መንገድ ነው፡፡ ይህ መንገድ "ኩሬውም እንዳይደርቅ አሳውም እንዳይሞት"

እንደሚባለው ለዘላቂ ሰላም መስፈን ሲባል የአከባቢውን ማህበረሰብ እሴት በጠበቀ ሁኔታ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ በዚህም ሁኔታ አሸናፊው ፍትህ እንጂ ግለሰብ አለመሆኑን በማስረገጥ ይጠናቀቃል፡፡

ተግባር 4.5

1. ይህ ማለት ከሳሽና ተከሳሽ አሸናፊ የሚሆኑበት ሲሆን በዚህ መሰረት የሚያሸንፈው ፍትህ እንጂ ግለሰብ አይደልም፡፡
2. በህብረተሰ የተከበሩ የአካባቢውን ባህል ጠንቅቀው የሚያቁ ታማኝና ለፍትህ የቆሙ አባቶች ናቸው፡፡
3. የችግሩ መንስዔና የህብረተሰቡ ዘላቂ ሰላም ናቸው፡፡
4. በባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ አሸናፊው ፍትህ ነው፡፡

ተግባር 4.6

1. እንዳይዋሹ ሲሆን ከዋሹ በህበረተሰቡ ዘንድ ታመኝነትን ስለሚያጡ ነው፡፡

ተግባር 4.7

1. ሀሰት ከተናገሩ ችግር ስለሚገጥማቸውና በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ስለሚያጡ፡፡
2. የግጦሹ መሬት የሁለቱም መሆኑን፡፡
3. በሀሰት ስለከሰሷቸው ነው፡፡
4. አሸናፊው ፍትህና የህብረተሱ ዘላቂ ሰላም ነው፡፡
5. ጉዳዩ በፍትህ ስለተቋጨና ወደነበረው ሰላማቸው ስለተመለሱ፡፡

ተግባር 4.8

1. ካለ "አዎ" ወይም ከሌለ "የለም"
2. የመደበኛ ፍርድ ቤት ምክንያቱም ረጅም ርቀት መሄድና ብዙ ውጣ ውረድ ስላለው ነው፡፡
3. ቃልኪዳንን ማፍረስ ጥሩ አለመሆኑን፡፡
4. የመደበኛ ፍርድ ቤት ስራ በይግባኝ ምክንያት ብዙ ውጣ ውረድ ያለውና ያልተገባ ወጪ የሚያሶጣ መሆኑን፡፡

## ትምህርት 4.4 የመረዳጃ ማህበራት/ተቋማት ማጠናከር (ቡሳ-ጎኖፋ)

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

☞ የህብረተሰቡን ችግሮችን ለመፍታት የቡሳ-ጎኖፋ ተቋም ሚናን ያደንቃሉ፤

☞ የማህበራዊ ችግር አፈታት ስልቶችን ይዘረዝራሉ፡፡

የትምህርቱ ይዘት

1. የመረዳጃ ማህበራት/ተቋማት ማጠናከር (ቡሳ-ጎኖፋ)

🕐 ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 5

**አጠቃላይ ገለፃ**

ይህ ትምህርት ስለቡሳ-ጎናፋ ማህበራት/ተቋማትን ማጠናከር ላይ ያተኩራል፡፡ቡሳ-ጎናፋ የኦሮሞ ማህበረሰብ አባላት በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ችግር ሲገጥማቸው የሚረዳዱባትና መልሰው የሚያቋቁሙበት ባህላዊ የመተጋገዣ ዘዴ ነው፡፡ ለተማሪዎቹ የኦሮም ህዝብ በድንገተኛ አደጋ ህይወታቸው ችግር ውስጥ የገቡትን የማህበረሰቡን አባላት አፋጣኝ እርዳታ በመለገስ የተቸገሩትን ለመርዳት ምግብና የተለያዩ ቁሶችን በመሰብሰብ የተቸገሩትን ለመርዳት የሚያስችል የቆየ ባህል መሆኑን ለተማሪዎች ያብራሩላቸው፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

መምህር፣ ከዚህ በታች ያሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡ እነሱም፡-

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤
- ☞ ስለ ዕለቱ ትምህርት አጭር ማብራሪያ መስጠት፤
- ☞ በመማር በማስተማር ሂደት ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤
- ☞ የቡድን ውይይቶችን ማካሄድ ሊሆን ይችላል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

መምህር፣ ወደ ክፍል ከመግባቶ በፊት አስፈላጊውን የትምህርት መርጃ መሳሪዎች ማዘጋጀት አለቦት፡፡ የዕለቱን ትምህርት ለመረዳት ከዚህ ርዕስ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ መጽሃፎችን ማንበብ ወይም የተማሪን መፃህፍና የመምህሩን መምሪያ ማንበብ አስፈላጊ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ሂደት

### 1. መግቢያ

መምህር፣ ስለ ቡሳ ጎኖፋ መረዳጃ ተቋማት ሚና አጭር መግቢያ በመስጠት ትምህርቱን መጀመር ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ቡሳ ጎኖፋ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ ያለዉን ሚና ማብራራት ይችላሉ፡፡ እንዲሁም የተቋሙን ጥቅም ጥቅሞ ለተማሪዎች በማብራራት የእለቱን ትምህርት መጀመር ይችላሉ፡፡ ወይም

- ☞ የትምህርቱን አላማ ለተማሪዎች በማብራራት፤
- ☞ የቡሳ ጎኖፋ ሚናን በመግለጽ፤
- ☞ ተማሪዎችን ስለቡሳ ጎኖፋ የግንዛቤ ጥያቂ በመጠየቅ ሊሆን ይችላል፡፡

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር ፣በመጀመሪያ ስለ ቡሳ ጎኖፋ ምንነት አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠት ተገቢ ነዉ፡፡ በመቀጠል ለተማሪዎች የቡሳ ጎኖፋ ተቋም በማህበራዊ ልማት ውስጥ ያለውን ሚና ይግለጹላቸው፡፡ እንዲሁም ቡሳ ጎኖፋ በህበረተሰቡ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ያለውን ሚና ለተማሪዎች የውይይት ጥያቄዎችን ይስጡ፡፡ በመጨረሻም የቡሳ ጎኖፋ አስፈላጊነት ተማሪዎችን በማደራጀት የመወያያ ጥያቄ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ማዳበር ይችላሉ፡፡

### 3. ማጠቃለያ

የዕለቱን ትምህርት ዋና ዋና ሃሳቦች ማለትም ስለቡሳ ጎኖፋ ያላቸው ግንዛቤ ለመረዳት የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን ማጠናቀቅ ይችላሉ፡፡

### 4. ክትትል እና ግምገማ

#### ሀ) ክትትል

ተማሪዎቹ ትምህርቱን ምን ያህል እንደተረዱት ለማወቅ የቤት ስራ፣ የክፍል ተሳትፎዎች ወይም የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መከታተል ይችላሉ፡፡

#### ለ) ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተረዱት ለማወቅ የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ወይም የተለያዩ መልመጃዎችን በመስጠት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህም የውይይት ጥያቄዎችን መስጠት እንዲሁም ከአቻዎቻቸው ጋር እንዲወያዩ በማበረታታት ወይም ከራሳቸው ምሳሌ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሀሳብ እንዲለዋወጡ በማድረግ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ፡ :

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

ተግባር 4.9

1. የተማሪዎችን ሀሳብ በማቀናጀት የአካባቢውን የመረዳዳት ባህል ያብራሩላቸው፡

ተግባር 4.10

1. ካለ አዎ ከሌለ የለም ብለው እንዲመልሱ ካደረጉ በኋላ ፣አለ ካሉ የሚያውቁትን እንዲያብራሩ ያድርጉ፡፡
2. የተማሪዎችን ሪፖርት በማዳመጥ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## ትምህርት 4.5. ኢኮኖሚ እንቅስቃሴን የሚያጠናክሩ ተቋማት (ቁጠባና ግብር)

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- የግብርን ምንነት ይገልጻሉ፤
- የግብር መክፈል አስፈላጊነትን ያብራራሉ፤
- የቁጠባን ምንነት ይገልጻሉ፤
- ቁጠባ በኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ያለውን ሚና ያብራራሉ፤
- የቁጠባ ተቋም አይነቶችን ይዘረዝራሉ፡፡

**የትምህርቱ ይዘት**

1. ኢኮኖሚ እንቅስቃሴን የሚያጠናክሩ ተቋማት

ለዚህ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት፡2

**አጠቃላይ ገለፃ**

ይህ ትምህርት ስለ ግብርና የቁጠባ ባህልን በማብራራት ይጀምራል፡፡ በመቀጠል ስለ ግብር ምንነት፣ግብር የመክፈል አስፈላጊነት ያብራራል፡፡ ግብር ማለትዜጎች የተለያዩ አገልግሎቶችን እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ ንጹህ ውሃ፣ መብራ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ መንገድና የመሳሰሉትን መንግስት እንዲያቀርብላቸው የሚረዳ ነው፡፡ በሌላ በኩል የቁጠባ ምንነት፣ የቁጠባ አይነቶችና ቁጠባ በኢኮኖሚ እድገት ላይ ያለውን ሚና የሚገልጽ ነው፡፡ ስለዚህ ግብር የመክፈልና የቁጠባን አስፈላጊነት ለተማሪዎች ማብራሪያ በመስጠት መጀመር ይችላሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ ለመማር ማስተማር የተመረጡ  ዘዴዎች

መምህር፣ ከዚህ በታች ያሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡ እነሱም፡-

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤
- ☞ ስለ ዕለቱ ትምህርት አጭር ማብራሪያ መስጠት፤
- ☞ በመማር በማስተማር ሂደት ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤
- ☞ የቡድን ውይይቶችን ማካሄድ ሊሆን ይችላል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

መምህር፣ ወደ ክፍል ከመግባቶ በፊት አስፈላጊውን የትምህርት መርጃ መሳሪዎች  ማዘጋጀት አለቦት፡፡ የዕለቱን ትምህርት ለመረዳት ከዚህ ርዕስ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ መጽሃፎችን ማንበብ ወይም የተማሪን መፃህፍና የመምህሩን መምሪያ ማንበብ አስፈላጊ ነው፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**1. መግቢያ**

መምህር፣ ስለ ግብርና ቁጠባ  አጭር መግቢያ በመስጠት ትምህርቱን መጀመር ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ግብርን መክፈልና የቁጠባ ባህል  በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ ያለዉን ሚና ማብራራት ይችላሉ፡፡ እንዲሁም የግብርና የቁጠባ  ጥቅሞች ለተማሪዎች በማብራራት የእለቱን ትምህርት መጀመር ይችላሉ፡፡ ወይም

- ☞ የትምህርቱን አላማ ለተማሪዎች በማብራራት፤
- ☞ ግብር የመክፈል አስፈላጊነት በመግለጽ፤
- ☞ የቁጣብን አስፈላጊነት ማብራራት ወይም
- ☞  ለተማሪዎችን ስለግብርና ቁጠባ የግንዛቤ ጥያቄ በመጠየቅ ሊሆን ይችላል፡፡

2. **የትምህርቱ አቀራረብ**

መምህር ፣በመጀመሪያ ስለ ግብር  ምንነት፣ የቁጠባ አስፈላጊነት  ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በመቀጠል ለተማሪዎች የግርና የቁጠባ ተቋማት በማህበራዊ ልማት ውስጥ ያለውን ሚና ይግለጹላቸው፡፡ እንዲሁም ቁጠባ በህበረተሰቡ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ያለውን ሚና ለተማሪዎች የውይይት ጥያቄዎችን ይስጡ፡፡

**3. ማጠቃለያ**

የዕለቱን ትምህርት ዋና ዋና ሃሳቦች ማለትም ስለግብር መክፈልና ቁጠባ አስፈላጊነት የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመረዳት የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን ማጠናቀቅ ይችላሉ፡፡

**4. ክትትል እና ግምገማ**

**ሀ) ክትትል**

ተማሪዎቹ ትምህርቱን ምን ያህል እንደተረዱት ለማወቅ የቤት ስራ፣ የክፍል ተሳትፎዎች ወይም የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መከታተል ይችላሉ፡፡

**ለ) ግምገማ**

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተረዱት ለማወቅ የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ወይም የተለያዩ መልመጃዎችን በመስጠት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህም የውይይት ጥያቄዎችን መስጠት እንዲሁም ከአቻዎቻቸው ጋር እንዲወያዩ በማበረታታት ወይም ከራሳቸው ምሳሌ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሀሳብ እንዲለዋወጡ በማድረግ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ፡፡

የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 4.11

1. ማንኛውም ሰው ከሚያገኘው ገቢ ላይ ለመንግስት የሚከፍለው ገንዘብ ነው፡፡
2. ዜጎች የተለያዩ አገልግሎቶችን እንደ ትምህርት፣ጤና፣ ንጽሁ ውሃ፣ መብራት፣ ቴሎኮምንኬሽን መንገድና የመሳሰሉትን አገልግሎት ለማግኘት ግብር ይከፍላሉ፡፡

ተግባር 4. 12

1. ቁጠባ ማለት የገቢና የወጪ ሚዛን በመጠበቅ ከሚገኘው ገቢ ላይ ለወደፊት ህይወት ለማሻሻል የሚቀመጥ ሃብት ነው፡፡
2. የቁጠባ ተቋማት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ዘመናዊና ባህላዊ የቁጠባ ተቋማት በመባል ይታወቃሉ፡፡ ዘመናዊ የቁጠባ ተቋማት የሚባሉት እንደ ባንክ፣ ኢንሹራንስና የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ያሉትን ያካትታል፡፡ባህላዊ የቁጠባ ተቋማት የሚባሉት እንደ ቡሳ ጎኖፋ ዊጆ (ሴቶች እርስ በርሳቸው የሚረዳዱበት) እንዲሁም እንደ እቁብ መረዳጃ ዕድርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
3. ከቁጠባ ጥቅሞች ጥቂቶቹ፡-
    - የወደፊት ፍላጎቶችን ለማሟላት (ለምሳሌ ትምህርት፣መኖሪያ ቤት፣ ወዘተ.)፤

- ተጨማሪ ገቢ ለመፍጠር፤
- ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመቋቋም፤
- በእርጅና ዘመን የሰው እጅ ከማየት ለመዳን ይጠቅማል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ

*መመሪያ አንድ፡ የ "እውነት" ወይም "ሐሰት" መልስ፡፡*

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት
6. ሐሰት
7. እውነት

*መመሪያ ሁለት፡ የምርጫ ጥያቄዎች መልስ*

| | |
|---|---|
| 1) መ | 3) ለ |
| 2) መ | 4) መ |

*መመሪያ፡ ሶስት፡ አጭር መልስ*

1. ችግኝ መትከል፣አቅመ ደካሞችን መርዳት፣የተለያዩ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
2. የወደፊት ፍላጎትን ለሟሟላት (ለምሳሌ ትምህርት፣ መኖሪያ ቤት)፣ተጨማሪ ገቢ ለመፍጠር፣ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋን ለመቋቋም፡፡
3. መ/ር/ት፡- ከ3 እስከ 5 ለቀረቡት ጥያቄዎች መብራሪያ ስጥዋቸው፡፡

# ምዕራፍ 5፡ የሀገር ፍቅር

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ስለ ሀገር ፍቅር ምንነት ፣ የሀገር ፍቅር መገለጫዎች፣ የሀገር ፍቅር አስፈላጊነት ፣ የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሚያሳዩትው ባህሪያት እንዲሁም ሀገርን መውደድ በሚሉ ርዕሶች ላይ ያተኮረ ሲሆን በእነዚህ ርዕሶች ስር የሚሰጡ ማብራሪያዎች ተማሪዎች ስለ ሀገር ፍቅር ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር በተግባር እንዲገልፁ የሚረዳቸው ፅንሰ ሃሳቦች ናቸው፡፡

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ☞ ስለ ሀገር ፍቅር ምንነት መግለጽ፤
- ☞ የሀገር ፍቅር መገለጫዎችን መዘርዘር፤
- ☞ የሀገር ፍቅር መላበስ አስፈላጊነትን መግለጽ፤
- ☞ የሀገር ፍቅር የተላበሱ ሰዎች የሚያሳዮቸውን ባህሪያት በተግባር ማሳየት፡፡

🕐 **ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 19**

## የምዕራፉ የትምህርቱ ይዘቶች

ትምህርት 1፡ የሀገር ፍቅር ምንነት

ትምህርት 2: የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎች

ትምህርት 3: የሀገር ፍቅር አስፈላጊነት

ትምህርት 4: የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ባህሪያት

ትምህርት 5: ሀገርን መውደድ

## ትምህርት 5.1. የሀገር ፍቅር ምንነት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- ☞ የሀገር ፍቅር ምንነት ይገልፃሉ፤
- ☞ የሀገር ፍቅርን በተግባር ያሳያሉ፡፡

የትምህርቱ ይዘት፡

1. የሀገር ፍቅር ምንነት

🕐 ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡3

**አጠቃላይ ገለፃ**

በዚህ የትምህርት ውስጥ ስለ ሀገር ፍቅር ምንነት ፣የሀገር ፍቅር ትርጉም አንድ ሰው ስለ ሀገሩ ያለውን ጥልቅ ፍቅርና እምነት የሚገልፅበት ነው፡፡ ይህም ማለት ሀገሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በጉልበት፣ በኢኮኖሚ፣ በእውቀት፣ በቴክኒክና በመሳሰሉት ሀገሩን በመርዳት በሀገሩ ላይ ተጨባጭ ልማት ፣እድገት እና የዜጐችን እኩልነት ማረጋገጥ እንደሆነ በመግለፅ ለተማሪዎች ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ መምህር በመቀጠልም የሀገር ፍቅር የሚገለፁባቸውን መንገዶች በመጥቀስና የተለዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ትምህርት ተጨባጭ ለማድረግ መሞክር ተገቢ ነው፡፡ .

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

መምህር፣ ከታች የተዘረዘሩትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ያሏቸውን የተለያዩ ፍላጎቶች በተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች መፍታት ይችላሉ፡፡ለምሳሌ

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄ መጠየቅ
- ☞ ማብራሪያ መስጠት
- ☞ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ
- ☞ በድራማ መልክ ማስተማርና የመሳሰሉትን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

የዕለቱን ትምህርት ከመጀመርህ/ሽ በፊት ለትምህርቱ ማሳለጫ የሚያገለግሉ አሰፈላጊ የሆኑትን የትምህርት መረጃ መሳሪያዎችን እንዲሁም ለመማርና ማስተማር አስፈላጊ የሆኑትን መሳሪያዎች ለምሳሌ እንደ እቅድ፣ ወረቀት፣ የዋቢ መፅሀፍት፣ እስክሪብቶና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

በዕለቱ በሚሰጠው የትምህርት ይዘት በመመስረት የራስዎትን ማስታወሻ በማዘጋጀት እንዲሁም ከዕለቱ የትምህርት ይዘት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዋቢ መፅሀፍትን በማንበብ ይዘጋጁ፡፡

## የመማር ማስተማር ሂደት

### 1. መግቢያ

መምህር፣ በእለቱ የትምህርት ይዘት ላይ በመመስራት ማለትም ሰለሀገር ፍቅር ምንነት አጠር ያለ ማብራሪያ ለተማሪዎች መስጠት ይጠበቅቦታል፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎቹ፡-

☞ ከተማሪ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን ይንገሯቸው፡፡

☞ የተማሪዎቹን በእለቱ ትምህርት ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹን ይጠይቁ፡፡ ለምሳሌ ኢትዩጲያዊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለክፍል ያስረዱ፡፡

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

የእለቱ የትምህርት ውይይት  ሰለሀገር ፍቅር ምንነት የተያዩ ምሳሌዎችን በማንሳትና በክፍል ውስጥ እንዲወያዩባችው በማድረግ የእለቱን ትምህርት መጀመር ይጠበቅቦታል፡፡

### 3. ማጠቃለያ

የዕለቱን የትምህርት ይዘት ማለትም ሰለሀገር ፍቅር አስመልክቶ አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማስታውስ የእለቱን የትምህርት ተጨባጭ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ ሰለአገር ፍቅር ምንነትን፡፡

### 4. ክትትል እና ግምገማ

**ሀ. ክትትል**

ስለሀገር ፍቅር አስመልክቶ ለተማሪዎች ጥያቄዎችን በማዘጋጀት እና ተማሪዎቹን በቡድን በማደራጀት በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የውይይቱን ሂደት በመከታተል አሰፈላጊውን እገዛ ያድረጉ፡፡ በመቀጠልም የተወያዩበትን ሃሳብ ለክፍሉ እንዲገልፁ ያበረታቱ፡፡ በገለጻቸው ወቅት ስህተቶች ካሉ ስህተቶችን ማረም አሰፈላጊ ነው፡፡ በመጨረሻም ለተማሪዎቹ የእለቱን ትምህርት አስመልክቶ የሚሰጡትን ነጥቦች ተማሪዎቹ በትክክል መያዛቸውን መከታተል ይችላሉ፡፡

ለ. ግምገማ

ተማሪዎቹ ሰለሀገር ፍቅር ምንነት ምን ያህል እንደተገነዘቡ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የእለቱን ትምህርት በትክክል መገንዘባቸውን ለማወቅ የቃል ጥያቄ፣  የክፍል ስራ፣ የተለያዩ ሙከራዎችን በመስጠት መገምገም ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹን ስለ ለሀገር ፍቅር ምንነት በቡድን  እንዲወያዩ በማበረታታት  በሀገር ፍቅር ዙሪያ ያ የራሳቸውን ምሳሌ / እንዲያቀረቡ በማድረግ መገምገም ይችላሉ፡፡

የተግባር የጥያቄዎች መልስ

ተግባር 5.1

1. የሀገር ፍቅር ማለት አንድ ሰው ስለ ሀገሩ ያለውን ጥልቅ ፍቅርና እምነት የሚገልፅበት ነው፡፡ ይህም ማለት ሀገሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በጉልበት፣ በኢኮኖሚ፣ በእውቀት፣ በቴክኒክ እና በመሳሰሉት አገሩን በመርዳት በሀገሩ ላይ ተጨባጭ ልማት፣ ብልፅግና እና የዜጐችን እኩልነት ማረጋገጥን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ለሕግ እና ለሕገ መንግሰትም መከበር አሰተዋጽኦ ማድረግንም ይገልጻል፡፡

2.

- ሰንደቅ አላማን ያከብራሉ፡፡
- ብሔራዊ መዝሙር ይዘምራሉ፡፡
- የጀግኖች ታሪክን በማክበርና በማስከበር ይታወቃሉ፡፡
- የህብረተሰብን የዕለት ከእለት ኑሮ የሚለውጡ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡
- የአንድን ሀገር ባህል፣ ታሪክ ለማወቅና በሥራ ላይ ለመተግበር ይጣጣራሉ፡፡
- የሀገር ፍቅር ያላቸዉ ዜጎች የአገራቸውን ስኬት እና እድገትን እንደራሳቸው ስኬትና እድገት ይቆጥራሉ፡፡

ተግበር 5.2

1

ለምሳሌ፡-

- አትሌት ሻንበል አበበ ቢቂላ ያሳለፋቸውን ውጣውረዶች አንድ በአንድ በማንሳት ለተማሪዎች አስፈላጊ እውቀትን አስገንዝቡ፡፡
- የአትሌት ሻንበል አበበ ቢቂላ ቆራጥነት ለዛሬው ትውልድ ምን እንዲያስጨብጥ እንዲሁም ከጉዳይ ጥናቱ ጋር የተያያዙ ምሳሌዎችን በማንሳት የጉዳይ ጥናቱን ጭብጥ ሃሳብ ተማሪዎቹ እንዲገነዘቡ ያድርጉ፡፡

## ትምህርት 5.2. የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎች

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- የዜጐችን የሀገር ፍቅር መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤
- የሀገር ፍቅርን በተግባር ያሳያሉ፡፡

የትምህርቱ ይዘት

## 1. የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎች

🕐 ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 5

**አጠቃላይ ገለፃ**

ይህ የትምህርት ክፍል ስለ ሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎች የሚነሳ ሲሆን እነሱም ዜጎች በሀገራቸው ታሪክ እና ባህል ይኮራሉ፤ ሀገራዊ ስሜትን ይላበሳሉ፤ ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ይጠየፋሉ፤ ለሀገር ክብር ይሰጣሉ፤ የሀገር ሉአላዊነትን ያስጠብቃሉ የሚሉትን ያካትታል፡፡እነዚህን በመግለፅ ለተማሪዎች ማብራሪያ ይሰጧቸው ፡፡ በመቀጠልም የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች እንደ ምሳሌ ይሆናሉ ብለን ያመንባቸውን ሰዎች በማነሳት ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት የእለቱን ትምህርት ተጨባጭ ለማድረግ መሞከር ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

**የመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች**

መምህር/ት፣ ከታች የተዘረዘሩትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ይችላሉ፡፡ለምሳሌ

- የግንዛቤ ጥያቄ መጠየቅ
- ማብራሪያ መስጠት
- በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ
- በድራማ መልክ ማስተማርና የመሳሰሉትን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

የዕለቱን ትምህርት ከመጀመርህ/ሽ በፊት ለትምህርቱ ማሳለጫ የሚያገለግሉ አሰፈላጊ የሆኑትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንዲሁም ለመማርና ማስተማር አስፈላጊ የሆኑትን መሳሪያዎች ለምሳሌ እንደ እቅድ፣ ወረቀት፣ የዋቢ መፅሀፍት፣ እስክሪብቶ፣ የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

በዕለቱ በሚሰጠው የትምህርት ይዘት በመመስረት የራስዎትን ማስታወሻ በማዘጋጀት እንዲሁም ከዕለቱ የትምህርት ይዘት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዋቢ መፅሀፍትን በማንበብ ይዘጋጁ፡፡

## የመማር ማስተማር ሂደት

**1. መግቢያ**

የእለቱ ትምህርት ይዘት ላይ በመመስረት የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎችን አጠር ያለ ማብራሪያ ለተማሪዎች መስጠት ይጠበቅቦታል፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎቹ፡-

☞ ከተማሪ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን ይንገሯቸው፡፡

☞ ተማሪዎቹን በእለቱ ትምህርት ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹን ይጠይቁ፡፡ ለምሳሌ ሰዎች የሀገራቸውን ፍቅር እንዴት ሊገልጹ ይችላሉ?

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎችን የተያዩ ምሳሌዎችን በማንሳትና በክፍል ውስጥ እንዲወያዩባችው በማድረግ የእለቱን ትምህርት መጀመር ይጠበቅቦታል፡፡

3. ማጠቃለያ

የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎችን አስመልክቶ አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማስታውስ የእለቱን የትምህርት ተጨባጭ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎችን በማንሳት፡፡

**4. ክትትል እና ግምገማ**

ሀ. ክትትል

የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎችን አስመልክቶ ለተማሪዎች ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና ተማሪዎቹን በቡድን በማደራጀት በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የውይይቱን ሂደት በመከታተል አስፈላጊውን እገዛ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም የተወያዩበትን ሃሳብ ለክፍሉ እንዲገልፁ ያድረጉ፡፡ በገለጻቸው ወቅት ስህተቶች ካሉ ስህተቶችን ማረም አስፈላጊ ነው፡፡

በመጨረሻም ለተማሪዎቹ የእለቱን ትምህርት አሰመልክቶ የሚሰጡትን ነጥቦች ተማሪዎቹ በትክክል መያዛቸውን ይከታተሉ፡፡

ለ. ግምገማ

ተማሪዎቹ የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጐች መገለጫዎችን አስመልክቶ ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማረጋገጥ ፡-የእለቱን ትምህርት በትክክል መገንዘባቸውን ለማወቅ የቃል ጥያቄ ፣ የክፍል ስራ፣ የተለያዩ ሙከራዎችን በመስጠት መገምገም ይችላሉ፡፡

የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 5.3

1.

- በሀገራቸው ታሪክ እና ባህል ይኮራሉ፤
- ሀገራዊ ስሜትን ይላበሳሉ፤
- ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ይጠየፋሉ፤
- ለሀገር ጀግኖች ክብር ይሰጣሉ፤
- የሀገር ሉአላዊነትን ያስጠብቃሉና የመሳሰሉት ናቸው።

2. መ/ር/ት፡-የሀገር ፍቅር መገለጫ መንገዶችን ለተማሪዎች አብራሩላቸው።

## ትምህርት 5.3. የሀገር ፍቅር አስፈላጊነት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

- በዜጎች ዘንድ የሀገር ፍቅር መኖር ለሀገር ያለውን ጥቅም ይገልፃሉ፤
- ለሀገራቸው ልዩ ፍቅር ይሰጣሉ።

የትምህርቱ ይዘት:

1. የሀገር ፍቅር አስፈላጊነት

ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡5

አጠቃላይ ገለፃ

በዚህ የትምህርት ውስጥ የሀገር ፍቅር አስፈላጊነትን በመግለፅ ለተማሪዎቸ ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል። በመቀጠልም የሀገር ፍቅር አስፈላጊነት በግለሰብና በሀገር ደረጃ ያለውን ጥቅም በማንሳት ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት የእለቱን ትምህርት ተጨባጭ ለማድረግ መሞከር ተገቢ ነው።

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

**ለመማር ማሰተማር የተመረጡ ዘዴዎች**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የመማር ማሰተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ።

ለምሳሌ፡-

- የግንዛቤ ጥያቄ መጠየቅ

- ማብራሪያ መስጠት
- በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ
- በድራማ መልክ ማስተማርና የመሳሰሉትን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

**ቅድመዝግጅት**

ለእለቱ ትምህርት ማሳለጫ የሚያገለግሉ አስፈላጊ የሆኑትን የትምህርት መረጃ መሳሪያዎችን እንዲሁም ለመማርና ማስተማር አስፈላጊ የሆኑትን መሳሪያዎች ለምሳሌ እንደ እቅድ ፣ ወረቀት፣ የዋቢ መፅሀፍት፣ እስክሪብቶና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**1. መግቢያ**

በእለቱ የትምህርት ይዘት ላይ በመመስራት ስለ አገር ፍቅር አስፈላጊነት አጠረ ያለ ማብራሪያ ለተማሪዎች መስጠት ይጠበቅቦታል፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎቹ፡-

☞ የመማር ብቃቶችን ያብራሩላቸው፡፡

☞ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ይጠይቁ፡፡

**2. የትምህርት አቀራረብ**

የሀገር ፍቅር አስፈላጊነትን የተያዩ ምሳሌዎችን በማንሳትና በክፍል ውስጥ እንዲወያዩባችው በማድረግ የእለቱን ትምህርት መጀመር ይጠበቅቦታል፡፡

**3. ማጠቃለያ**

የሀገር ፍቅር አስፈላጊነት አስመልክቶ አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማስታውስ የእለቱን የትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

4. ክትትል እና ግምገማ

ሀ. ክትትል

☞ ስለሀገር ፍቅር አስፈላጊነት አስመልክቶ ለተማሪዎች ጥያቄዎችን በማዘጋጀት እና ተማሪዎቹን በቡድን በማደራጀት በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የውይይቱን ሂደት በመከታተል አስፈላጊውን እገዛ ይስጧቸው፡፡

በመጨረሻም ለተማሪዎቹ የእለቱን ትምህርት አስመልክቶ የሚሰጡትን ነጥቦች ተማሪዎቹ በትክክል መያዛቸውን ይከታተሉ፡፡

ለ. ግምገማ

☞ ተማሪዎቹ የሀገር ፍቅር አስፈላጊነትን አስመልክቶ ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ የቃል ጥያቄ ፣ የክፍል ስራ ፣የተለያዩ ሙከራዎችን በመስጠት ይገምግሙ፡፡

የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 5.4

1.

- ዜጐች ከሀገራቸው የተለየያዩ ጥቅሞችን እንዲያገኙ ያደረጋል፡፡
- ሀገራዊ ስሜት እንዲሰማቸው ያደረጋቸዋል፡፡
- በሀገር ጉዳይ ዜጎች ተባብረው በአንድነት እንዲሰሩ ያደረጋል፡፡
- ዜጐች ሀገራቸውን ለውጭ ጠላት እንድትጋለጥ ይሰራሉ፤
- የሀገር አንድነትን ያሰጠብቃል፤
- እድገትን ያመጣል፤
- ብሄራዊ አንድነትን ይፈጥራል እና የመሳሰሉትን ማንሳት ይቻላል፡፡

## ትምህርት 5.4. የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ባህሪያት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃት፡-

☞ የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጎች ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፡፡

የትምህርቱ ይዘት

1. የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ባህሪያት

🕐 ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡2

**አጠቃላይ ገለፃ**

በዚህ ትምህርት ውሰጥ የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ባህሪያት አንድ በአንድ በማንሳት ለተማሪዎቸ ማብራሪያ ይሰጧቸው፡፡ በመቀጠልም የሀገር ፍቅር ያላቸውን ሰዎች ባህሪያት በምሳሌ አስረዷቸው፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴ

የትምህርት መርጃ መሳሪያ

ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

ከታች የተዘረዘሩትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡ለምሳሌ

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄ መጠየቅ
- ☞ ማብራሪያ መስጠት
- ☞ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ
- ☞ በድራማ መልክ ማስተማርና የመሳሰሉትን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

ቅድመ ዝግጅት

ለትምህርቱ ማሳለጫ የሚያገለግሉ አሰፈላጊ የሆኑትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንዲሁም ለመማርና ማስተማር አስፈላጊ የሆኑትን መሳሪያዎች ለምሳሌ እንደ እቅድ ፣ ወረቀት፣ የዋቢ መፅሀፍት፣ እስክሪብቶና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

የመማር ማስተማር ሂደት

1. መግቢያ

የሀገር ፍቅር አስፈላጊነትን አጠር ያለ ማብራሪያ ለተማሪዎች መስጠት ይጠበቅቦታል፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎቹ፡-

- ☞ የመማር ብቃቶችን ያብራሩላቸው፡፡
- ☞ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹን ይጠይቁ፡፡

2. የትምህርት አቀራረብ

የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎችን ባህሪያት ምሳሌዎችን በማነሳትና በክፍል ውስጥ እንዲወያዩባችው በማድረግ የእለቱን ትምህርት መጀመር ይጠበቅቦታል፡፡

3. ማጠቃለያ

የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሚያሳዩትን ባህሪያት አስመልክቶ አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማስታውስ የእለቱን ትምህርት ማጠቃለል ያስፈልጋል፡፡

**4. ክትትል እና ግምገማ**

ሀ. ክትትል

- ☞ የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሚያሳዩዋቸው ባህሪያት ለተማሪዎች ጥያቄዎችን በማዘጋጀት በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የቡድን የውይይቱን ሂደት በመከታተል አሰፈላጊውን እገዛ ያድረጉ፡፡ በገለጻቸው ወቅት ስህተቶች ካሉ ስህተቶችን በማረም መከታተል ይችላሉ፡፡

- ☞ በመጨረሻም ለተማሪዎቹ የእለቱን ትምህርት አስመልክቶ የሚሰጡትን ነጥቦች ተማሪዎቹ በትክክል መያዛቸውን ይከታተሉ፡፡

ለ. ግምገማ

- ☞ የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሚያሳዩቸውን ባህሪያት ምን ያህል እንደሚያዉቁ ለመረዳት የቃል ጥያቄ ፣ የክፍል ስራ ፣የተለያዩ ሙከራዎችን በመስጠት ግምገማ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሚያሳዩዋቸውን ባህሪያት በቡድን በማደራጀት እንዲወያዩ በማበረታታት እንዲሁም ባካባቢያቸው የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሚያሳዩዋቸውን ባህሪያት እንደምሳሌ እንዲያነሱ በመድረግ መገምጋም ይችላሉ፡፡

የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 5.5

1.

- ✍ በሀገሩ ባህል እና ታሪክ ይኮራል፡፡
- ✍ ለዜጐች እኩልነት፣ እድገት፣ ቀንና ለሊት በመስራት ለሀገር ጥቅም መሳካት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡
- ✍ ልጆች ሀገራቸውን እንዲያውቁና ለሀገራቸው ፍቅር እንዲሰጡ አድርጐ ያሳድጋል፡፡
- ✍ ለማህበረሰባቸው ይተጋሉ፡፡
- ✍ ለማህበረሰብ ሰላምና ጤና እንዲጠበቅ አበክረው ይሰራሉ፤ እነዚህንና ሌሎቹን ማንሳት ይቻላል፡፡

2.

- ☞ ለዜጎች መብት መከበር ይሰራሉ፤
- ☞ አቅመ ደካሞችን በመረዳት ላይ ይሳተፋሉ፤
- ☞ በትርፍ ጊዜያቸው የተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎችን ያከናውናሉ፤
- ☞ አከባቢን ከተለያዩ ብክለቶች ይጠብቃሉ፡፡ እነዚህንና ሌሎቹን ማንሳት ይቻላል፡፡

## ትምህርት 5.5. ሀገር መውደድ

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃት፡-

- ☞ ሀገርን የመውደድ አስፈላጊነትን ይገልጻሉ፡፡

የትምህርቱ ይዘት ፡

1. ሀገር መውደድ

🕐 ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 2

አጠቃላይ ገለፃ

በዚህ የትምህርት ይዘት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ስለሀገር መውደድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና የሀገርን መውደድ ጠቀሜታ እንዲሁም የሀገር ወዳድ ዜጎች ባህርያት ላይ ያተኩራል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ ጥልቅ እውቀት እንዲኖራቸው በቡድን በማደራጀት እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

☞ ከታች የተዘረዘሩትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

☞ ለምሳሌ፡-

- ☞ የግንዛቤ ጥያቄ መጠየቅ
- ☞ ማብራሪያ መስጠት
- ☞ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ
- ☞ በድራማ መልክ ማስተማርና የመሳሰሉትን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

ቅድመዝግጅት

ለትምህርቱ ማሳለጫ የሚያገለግሉ አስፈላጊ የሆኑትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንዲሁም ለመማር ማስተማር አስፈላጊ የሆኑትን መሳሪያዎች ለምሳሌ እንደ እቅድ ፣ ወረቀት፣ የዋቢ መፅሀፍት፣ እስክሪብቶና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

የመማር ማስተማር ሂደት

1. መግቢያ

ይህ የትምህርት ክፍል የሚጀምረው ተማሪዎች ስለ ሀገር መውደድ ያላቸውን ግንዛቤ በመጠየቅ ይሆናል፡፡ በመቀጠልም ለተማሪዎች ከትምህርቱ በኃላ ምን ማወቅ እንዳለባቸው መንገር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ተማሪው/ተማሪዋ፡-

- ☞ ከተማሪ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን ይንገሯቸው፡፡
- ☞ ተማሪዎቹን በእለቱ ትምህርት ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ይጠይቁ፡፡

2. የትምህርቱ አቀራረብ

የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሚያሳዩዋቸው ባህሪያት በማስታውስ እና የእለቱን ትምህርት በማስተዋወቅ ትምህርቱን ይጀምሩ፡፡ በተጨማሪም በእለቱ ትምህርት ላይ በማተኮር ማለትም ስለ ሀገርን መውደድ አጠረ ያለ ማብራሪያ ለተማሪዎች መስጠት ይጠበቅቦታል፡፡

3. ማጠቃለያ

የሀገር መውደድን አስመልክቶ አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማስታውስ የእለቱን የትምህርት ተጨባጭ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

4. ክትትል እና ግምገማ

ሀ. ክትትል

- ☞ ስለ ሀገር መውደድ አስመልክቶ ለተማሪዎች ጥያቄዎችን በማዘጋጀት እና ተማሪዎቹን በቡድን በማደራጀት በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የውይይቱን ሂደት በመከታተል አስፈላጊውን እገዛ ያድረጉ፡፡ በመቀጠልም የተወያዩበትን ሃሳብ ለክፍሉ እንዲገልፁ ያድረጉ፡፡ በገለጻቸው ወቅት ስህተቶች ካሉ ስህተቶችን ማረም አስፈላጊ ነው፡፡
- ☞ በመጨረሻም ለተማሪዎቹ የእለቱን ትምህርት አስመልክቶ የሚሰጡትን ነጥቦች በመከታተል ተማሪዎቹ በትክክል መያዛቸውን ይከታተሉ፡፡

ለ. ግምገማ

- ☞ ተማሪዎቹ የሀገር መውደድ ምንነት ምን ያህል እንደተገነዘቡ  ለማወቅ የቃል ጥያቄ ፣ የክፍል ስራ  ፣የተለያዩ ሙከራዎችን በመስጠት መገምገም ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹን ስለ ሀገርን መውደድ በቡድን በማደራጀት እና እንዲዎያዩ በማበረታታት እንዲሁም በአገር መውደድ  ዙሪያ ያላቸውን የራሳቸውን ተሞክሮ /ምሳሌ / እንዲያቀረቡ ያድረጉ፡፡

## የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 5.6

1. .

- በሀገር ታሪክና ባህል መኩራት፤
- ለሀገር ሰላምና እድገት መስራት፤ እንዲሁም ከምንም በላይ ሀገር ሰላም እና አድጋ ማየት መመኘትን ያጠቃልላል።

2.

ሀገርን መውደድ የተለያዩ ጥቅሞች አሉት ለምሳሌ፡-

- ህዝቦች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ለማስተሳሰር ወይም አንድ ለማድረግ ይጠቅማል።
- ጠንካራ ሀገረመንግስት ለመፍጠር ይረዳል።

5.7. መ/ር/ት፡- በዚህ ተግባር ስር ላሉት ጥያቄዎች መፀሃፉን በማንበብ ለተማሪዎች ማብራሪያ ይስጡ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ

መመሪያ አንድ፡- እውነት/ ሐሰት

1) እውነት
2) እውነት
3) እውነት
4) እውነት
5) እውነት

መመሪያ ሁለት፡- ምረጫ

1) መ 2) ሐ

መምሪያ፡ ሶስት፡- አጭር ማብራሪያዎች።

1. .

የሀገር ፍቅር ስሜት ማለት አንድ ሰው ስለ ሀገሩ ያለውን ጥልቅ ፍቅርና እምነት የሚገልፅበት ነው። ይህም ማለት ሀገሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በጉልበት፣ በኢኮኖሚ፣ በእውቀት፣ በቴክኒክ እና በመሳሰሉት አገሩን በመርዳት በአገሩ ላይ ተጨባጭ ልማት ፣ ብልፅግና እና የዜጐችን እኩልነት ማረጋገጥን ያካትታል። በተጨማሪም ለህግ እና ለህገመንግስትም መከበር አስተዋጽኦ ማድረግንም ይገልጻል።

2.

- መሪዎች ሙሉ አቅማቸውን በመጠቀም ለሀገር እንዲሰሩ ያግዛቸዋል፡፡
- ሙስናን አጥብቀዉ እንዲታገሉ ያደረጋቸዋል፡፡

3.

- ሰንደቅ አላማን ያከብራሉ፡፡
- ብሔራዊ መዝሙር ይዘምራሉ፡፡
- የጀግኖች ታሪክን በማክበርና በማስከበር ይታወቃሉ፡፡
- የህብረተሰብን የዕለት ከእለት ኑሮ የሚለውጡ ተግባራትን ያከናወናሉ፡፡
- የአንድን ሀገር ባህል፣ ታሪክ ለማወቅና በሥራ ላይ ለመተግበር ይጣጣራሉ፡፡
- የአገር ፍቅር ያላቸዉ ዜጎች የሀገራቸውን ስኬት እና እድገትን እንደራሳቸው ስኬትና እድገት ይቆጥራሉ፡፡

# ምዕራፍ 6፡ ሰላምና ህብረት

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ስለ ሰላም ምንነት፣ የሰላም አስፈላጊነት ስለህብረት ምንነት፣ አስፈላጊነት እንዲሁም በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት ላይ ያተኩራል። ተማሪዎች የሰላም አስፈላጊነትን እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል። ሰላም ማለት ጦርነት አልባ ወይም ብጥብጥ አልባ ማለት ነው። ስለዚህ ተማሪዎች ለሰላም ትልቅ ቦታ በመስጠት ለችግሮቻቸው መፍትሄ ለመፈለግ ጉልበትን ሳይሆን ምክንያታዊነትን እንዲሁም ከብጥብጥ ይልቅ ንግግረን ማስቀደም እንዳለባቸው ግንዛቤ ይፈጥርላቸዋል።

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች**

- ☞ ስለ ሰላም ምንነት መግለጽ፤
- ☞ የሰላም አስፈላጊነትን ማብራራት፤
- ☞ ስለ ህብረት ምንነት መግለጽ፤
- ☞ ለህብረት አስፈላጊነት ትልቅ ቦታ መስጠት፤
- ☞ የህብረትን እሴቶች መለማመድ ናቸው።

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ፡ 19

ይዘቶች

ትምህርት 1፡ የሰላም ምንነት

ትምህርት 2: ህብረት

ትምህርት 3: በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት

## ትምህርት 6.1. የሰላም ምንነት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃት፡-

- ☞ የሰላም ምንነትን ይገልፃሉ።

የትምህርቱ ይዘት ፡

1. የሰላም ምንነት

🕐 ለእዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 7

አጠቃላይ ገለፃ

ይህ ምዕራፍ ስለ ሰላም ምንነት፣ የሰላም አስፈላጊነት፣ እንዲሁም ስለህብረት ምንነት፣ አስፈላጊነት በተጨማሪም ተማሪዎች በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲገነዘቡ ያደረጋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ ጥልቅ እውቀት እንዲኖራቸው በቡድን በማደራጀት እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት ለተማሪዎቹ ጥያቄ በማቅረብ እንዲወያዩባቸው ማድረግ ይጠበቅቦታል ፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

ከታች የተዘረዘሩትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

- የግንዛቤ ጥያቄ መጠየቅ
- ማብራሪያ መስጠት
- በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ
- በድራማ መልክ ማስተማርና የመሳሰሉትን መጠቀም ይቻላል፡፡

ቅድመ ዝግጅት

ለትምህርቱ ማሳለጫ የሚያገለግሉ አሰፈላጊ የሆኑትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንዲሁም የመማርና ማስተማር አስፈላጊ የሆኑትን መሳሪያዎች ለምሳሌ እንደ እቅድ ፣ ወረቀት፣ የዋቢ መፅሀፍት፣ እስክሪብቶና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡እንዲሁም ከዕለቱ የትምህርት ይዘት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዋቢ መፅሀፍትን በማንበብ ይዘጋጁ፡፡

የመማር ማስተማር ሂደት

1. መግቢያ

   ይህ የትምህርት የሚጀምረው ተማሪዎች ስለ ሰለም ያላቸውን ግንዛቤ ጥያቄ በመጠየቅ ሊሆን ይችላል፡፡ በመቀጠልም ለተማሪዎች፡-

   - የመማር ብቃቶችን ይብራሩላቸው፡፡
   - ስለ ሰለም ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

ይህ ትምህርት ስለ ሰላም ምንነት ማብራሪያ በመስጠት መጀመር ይችላሉ፡፡በተጨማሪም ስለ ሰላም ምንነት ተገቢ ማስታወሻ በመስጠት ያብራሩላቸው፡፡

**3. ማጠቃለያ**

የእለቱን የትምህርት ይዘት ማለትም የሰላም ምንነትን አስመልክቶ አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማስታውስ የእለቱን ትምህርት ማጠናቀቅ ያስፈልጋል፡፡

**ክትትልና ግምገማ**

ሀ. ክትትል

- ☞ የሰላምን ምንነት አስመልክቶ ለተማሪዎች ጥያቄዎችን በማዘጋጀት እና ተማሪዎቹን በቡድን በማደራጀት በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የውይይቱን ሂደት በመከታተል አሰፈላጊውን እገዛ ይስጧቸው፡፡ በገለጻቸው ወቅት ስህተቶች ካሉ ስህተቶችን በማረም መከታተል ይችላሉ፡፡
- ☞ በመጨረሻም ለተማሪዎቹ የእለቱን ትምህርት አስመልክቶ የሚሰጡትን ነጥቦች በመከታተል ተማሪዎቹ በትክክል መያዛቸውን ይመልካቱ፡፡

ለ. ግምገማ

- ☞ ተማሪዎቹ ስለ ሰላም ምንነት ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማረጋገጥ የቃል ጥያቄ ፣ የክፊል ስራ ፣የተለያዩ ሙከራዎችን በመስጠት መገምገም ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹን ስለ ሰላም ምንነት በቡድን በማደራጀትና እንዲዎያዩ በማበረታታት እንዲሁም በሰላም ምንነት ዙሪያ ያላቸውን ተሞክሮ እንዲያቀረቡ ያድረጉበማድረግ መገምገም ይችላሉ፡፡

የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 6.1

1.

- ✍ ሰላም ማለት ጦርነት አልባ ወይም ብጥብጥ አልባ ማለት ነው፡፡

2.

- ✍ አዎ! ምክንያቱም ሁሉም ማህበረሰብ ሰላምን የማስጠበቅ ሃላፊነት ስላለበትና ተማሪዎች የማህበረስቡ አንድ አካል ስለሆኑ የሰላም ጉዳይ ይመለከታቸዋል ማለት ነው፡፡ ተማሪዎች በማህበረተሰቡ ዘንድ ለሰላም ጠንቅ የሆኑትን ተግባባራት እንደ

ያለድሜ ጋብቻን ማጥፋት ላይ መስራት፣ ብጥብጥን መቀነስ ላይ በመስራት የራሳቸውን አስተዋፅኦ ይወጣሉ፡፡

3.

- ግጭትና ጦርነት እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡
- ነፃነትእንዳይኖር ያደርጋል
- ለነፃነት ማጣት ትልቅ ምክንያት ይሆናል፡፡

## ትምህርት 6.2 ህብረት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃት፡-

- ስለ ህብረት ምንነት ይገልፃሉ፡፡

የትምህርቱ ይዘት፡

1. ህብረት

ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት ፡7

አጠቃላይ ገለፃ

በዚህ ትምህርት ውስጥ ስለ ህብረት ምንነት፣የህብረት አስፈላጊነትና የህብረት መርሆች ተካተዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ ጥልቅ እውቀት እንዲኖራቸው በቡድን በማደራጀት እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች
ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

- ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

ከታች የተዘረዘሩትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

- የግንዛቤ ጥያቄ መጠየቅ
- ማብራሪያ መስጠት
- በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ
- በድራማ መልክ ማስተማርና የመሳሰሉትን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ቅድመ ዝግጅት

ለትምህርቱ ማቀናጃ የሚያገለግሉ የትምህርት መረጃ መሳሪያዎችን እንዲሁም ለመማር ማስተማረ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን ለምሳሌ እንደ እቅድ ፣ ወረቀት፣ ዋቢ መፅሀፈት፣

እስክሪብቶና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በተጨማሪም የራስዎትን ማስታወሻ በማዘጋጀት እንዲሁም ከዕለቱ የትምህርት ይዘት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዋቢ መፅሀፍትን በማንበብ ይዘጋጁ።

የመማር ማስተማር ሂደት

1. መግቢያ

   ይህ የትምህርት ስለ ህብረት ምንና አስፈላጊነት ላይ ያተኩራል።በመሆኑም ተማሪዎች ስለ ህብረት ምንነትና አስፈላጊነት ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ጥያቄ በመጠየቅ መጀመር ይችላሉ።በመቀጠል ለተማሪዎቹ:-

   - የመማር ብቃቶችን ያብራሩላቸው።
   - ስለህበረት ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ጥያቄ ይጠይቁ።

2. የትምህርቱ አቀራረብ

ይህንን ትምህርት ስለ ህበረት አጠር ያለ ማብራሪያለተማሪዎቹ በመስጠት ይጀምሩ። በተጨማሪም በእለቱ ትምህርት ላይ በማተኮረ ስለ ህብረት ምንነት ማስታወሻ ለተማሪዎች መስጠት ይጠበቅቦታል።

3. ማጠቃለያ

ህብረትን አስመልክቶ አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማስታውስ የእለቱን የትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ።

4. ክትትል እና ግምገማ

ሀ. ክትትል

ሰለ ህብረት ምንነት፣ የህብረት አስፈላጊነት እና የህብረት መርሆችን አስመልክቶ ለተማሪዎች ጥያቄዎችን በመጠየቅና ተማሪዎቹን በቡድን በማደራጀት በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ። በመቀጠልም የውይይቱን ሂደት በመከታተል አሰፈላጊውን እገዛ ያድረጉ። በመቀጠልም የተወያዩበትን ሃሳብ ለክፍሉ እንዲገልፁ ያድረጉ። በገለጻቸው ወቅት ስህተቶች ካሉ ስህተቶችን በማረም መከታተል ይችላሉ።

ለ. ግምገማ

ተማሪዎቹ ስለ ህብረት ምንነት፣የህብረት አስፈላጊነት እና የህብረት መርሆችን በተመለከተ ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ የቃል ጥያቄ ፣ የክፍል ስራ ፣ የተለያዩ ሙከራዎችን በመስጠት መገምገም ይችላሉ።

የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 6.2

1.

- በህብረት መስራት ስራዎች እንዲቀላጠፉ በማድረግ እና በስራችን ደስተኝ እንድንሆን ያደረገናል፡፡
- በህዝቦች መካከል ያለውን መስተጋብር እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡

2.

- በህብረት ማጥናት
- በክበባት ውስጥ በጋራ መስራት
- በትምህርት ጉዳዮች ላይ ሀሳብን መለዋወጥ
- የትምህርት ማህበረስቡን በትምህርት ጉዳይ ላይ ማማከር የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

3.

- በሚሰጡት ውሳኔ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ስለሆኑ፤
- ከሰዎች ጋር ያላቸውን የመግባባት እና ችግሮችን የመፍታት ችሎታቸውን ስለሚጨር፤
- በቤተሰብና በመምህራን መካከል ያላቸውን ግንኙነት እጅጉን ሰለሚያጠናክርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ትምህርት 6.3. በሰላምና በህብረት መካከል ያለው ግንኘነት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃት፡-

በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን መስተጋብር ያደንቃሉ፡፡

የትምህርቱ ይዘት ፡

በሰላምና በህብረት መካከል ያለው ግንኘነት

🕐 ለዚህ ትምህርት የተሰጠዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡5

አጠቃላይ ገለፃ

ይህ ትምህርት በሰላምና በህብረት መካከል ያለው ግንኘነት ምን እንደሆነ በማብራራት ይጀምራል ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ ጥልቅ እውቀት እንዲኖራቸው በቡድን በማደራጀት እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡

የመማር ማሰተማር ዘዴ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ምስለ ድምፅ፣ ፎቶ/ምስል

☞ ለመማር ማስተማር የተመረጡ ዘዴዎች

ከታች የተዘረዘሩትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

እነሱም፡-

☞ የግንዛቤ ጥያቄ መጠየቅ

☞ ማብራሪያ መስጠት

☞ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ

☞ በድራማ መልክ ማስተማርና የመሳሰሉትን መጠቀም ይችላሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

ትምህርቱን ለማቀናጀት የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንዲሁም ለመማር ማስተማር አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች ለምሳሌ እንደ እቅድ ፣ ወረቀት፣ የዋቢ መፅሀፍት፣ እስክሪብቶና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

የመማር ማስተማር ሂደት

1. መግቢያ

ይህ የትምህርት ተማሪዎች በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት ምን ያህል እንደሚያወቁ በመጠየቅ ይሆናል፡፡ በመቀጠልም ለተማሪዎች ከትምህርቱ በኃላ ምን ማወቅ እንዳለባቸው መንገር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ማብራሪያ ለተማሪዎች መስጠት ይጠበቅቦታል፡፡

3. ማጠቃለያ

በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማስታውስ የእለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

4. ክትትል እና ግምገማ

ሀ. ክትትል

በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኘነት አስመልክቶ ተማሪዎችን ጥያቄዎች በመጠየቅና በቡድን በማደራጀት በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የውይይቱን ሂደት በመከታተል አሰፈላጊውን እገዛ ያድረጉ፡፡ ከዚያም የተወያዩበትን ሃሳብ ለክፍሉ እንዲገልፁ ያድረጉ፡፡ በገለጻቸው ወቅት ስህተቶች ካሉ ስህተቶችን በማረም ይከታተሉ፡፡

ለ. ግምገማ

በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተማሪዎቹ ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ የቃል ጥያቂ ፣ የክፍል ስራ ፣ የተለያዩ ሙከራዎችን በመስጠት ግምገማ አድርጉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹን በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኘነት በተመለከተ በቡድን በማደራጀትና እንዲዎያዩ በማበረታታት መገምገም ይችላሉ፡፡

የተግባር ጥያቄዎች መልስ

ተግባር 6.3

1.

- ማንኛውም ማህበረስብ ሰላምን ለማረጋገጥ በህብረት ወይም በጋራ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም ማለት ሰላም ያለ ህብረት በተወሰኑ ሰዎች ፍላጎት ብቻ የሚረጋገጥ አለመሆኑንና በሁለቱ መካከል ትልቅ መስተጋብር መኖሩን ያሳያል፡፡
- የግጭት፣ የጦርነት ምክንያቶች ሰላምን ለማረጋገጥ የህብራት አለመኖርን ያሳያል ፡፡ ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች የሰላምንና የሕብረት ግንኙነቶችን የሚገልፅ ናቸው፡፡

2.

- በጋራ መስራት፤
- አታክልትን በጋራ መትከል፤
- በትርፍ ሰአት መጫወት፤

3.

- እድገትና ልማትን ለማረጋገጥ ያግዛል፤
- ከጎሮቤት ሀገራት ጋር ጥሩ ግንኙነትን እንዲኖር ያደርጋል፤ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

**የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ**

**መመሪያ አንድ፡ እውነት/ ሐሰት**

**1.** ሐሰት **3.** ሐሰት **5.** ሐሰት

**2.** እውነት **4.** ሐሰት

**መመሪያ ሁለት፡ ምረጫ**

1) **ለ** 2) **ለ** 3) **መ** 4) **መ**

**መመሪያ 3 አጭር ማብራሪያዎች**

1.

- መተማመን ከሰዎች ጋር አብሮ ለመስራት ይረዳል፤
- መተማመን በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት/ህብረት/ ያጠናክራል፡፡

2.

- እርስ በራስ መረዳዳት፤
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በቡድን አብሮ መስራት፤
- አታክልትን መትከልና መንከባከብ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

3. የህብረት መርሆች የሚባሉትን ጥቂቶችን ጥቀስ/ሽ፡፡

- አንድነት፤
- ለሌሎች ሰዎች ማሰብ መቻል፤
- ግልጽነትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

# የ6ኛ ክፍል ግብረገብ ሲሌበስ

## ምዕራፍ 1፡ የታማኝነት መርሆች (የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት 19)

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፣

- የታማኝነት መርሆችን መግለጽ፤
- የታማኝነት መርሆችን ባህሪ በተግባር ማሳየት፤
- የታማኝነት መርሆችን አስፈላጊነት ማብራራት፤
- የታማኝነት መርሆች መገለጫ ባህሪያትን መዘርዘር፤
- የታማኝነት መርሆችን አለመተግበር የሚያስከትሏቸውን ችግሮች መለየት፡፡

| የመማር ውጤቶች | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ☞ የታማኝነትመርሆችን መግለፅ፤<br>☞ የታማኝነት መርሆ ባህሪያትን ማሳየት፤<br>☞ የታማኝነት መርሆች አስፈላጊነትን ማብራራት፤<br>☞ የታማኝነት መርሆ መገለጫ ባህሪያትን መዘረዘር፤<br>☞ የታማኝነትመርሆን አለመተግበር የሚያስከትሏቸውን ችግሮች መለየት፡ | 1.1 የታማኝነት መርሆች ምንነት፤<br>1.2 የታማኝነት መርሆች ባህሪያት፤<br>1.3 የታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት፤<br>1.4 የታማኝነት መርሆችን የተላበሱ ሰዎች ባህሪያት፤<br>1.5 የታማኝነት መርሆች ባለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮ | ♦ የታማኝነት መርሆ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎችን መጠየቅ<br>♦ ተማሪዎች የታማኝነት መርሆችን ባህሪያት እንዲዘረዝሩ መጠየቅ<br>♦ ተማሪዎች ስለ ታማኝነት መርሆች አስፈላጊነት ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች የታማኝ ሰው ባህሪያትን እንዲያብራሩ ማገዝ<br>♦ ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ ሆነው የታማኝነት መርሆዎችን አለመተግበር የሚያስከትላቸው ችግሮች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ስለ ታማኝነት መርሆች ለተማሪዎች የተለያዩ ታሪኮችን አቅርቦ ማብራራት<br>♦ ተማሪዎች ስለ ታማኝነት መርሆች የሚያውቁትን እንዲጽፉ ማድረግ | ♦ ተማሪዎች ስለ ታማኝነት መርሆች ምንነት እንዲያብራሩ መጠየቅ<br>♦ ተማሪዎች ሲወያዩ ከትምህርት ውጤቶች ጋር የተጣጣመ መሆኑን መከታተል<br>♦ ጥያቄና መልስ ማካሄድ<br>♦ ተማሪዎች የተጠየቁትን ሲመልሱ በመከታተል ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት<br>♦ የሙከራ ፈተናዎችን መስጠት |

**ምዕራፍ 2፡ ሕግ ማክበር** (የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት 20)

ከምዕራፉ የሚጠበቁ  የመማር ውጤቶች፤

- ☞ ሕግ የማክበር ምንነትን መግለጽ፤
- ☞ ሕግ የማክበር አስፈላጊነትን መዘርዘር፤
- ☞ ህግ አክባሪ ሰው የሚያሳያቸውን ባህሪያትን ማሳየት፤
- ☞ ህግን አለማክበር የሚያስከትለውን ችግር መግለፅ።

| የትምህርቱ ውጤት | ይዘት | የመማር ማስተማር ዘዴ | ክትትል |
|---|---|---|---|
| ♦ ሕግ የማክበር ምንነትን መግለፅ፤<br>♦ ሕግ የማክበር አስፈላጊነትን መዘርዘር፤<br>♦ የህግ አክባሪ ሰው ባህሪያት ላይ ጽብረቃ ማቅረብ፤<br>♦ ህግ አለማክበር የሚያስከትለውን ችግር መግለፅ። | 2.1. ሕግ የማክበር ምንነት<br>2.2. ሕግ የማክበር አስፈላጊነት<br>2.3. የሕግ አስከባሪ ሰው ባህሪያት<br>2.4. ህግን አለማክበር የሚያስከትለው ችግር | ♦ ተማሪዎች ቡዝ (buzz group) የሚባለውን በቡድን የመስራት ዘዴን በመጠቀም ስለ ህግ ምንነት እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች በቡድን ሆነው ህግ የማክበር አስፈላጊነትን እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ የጉዳይ ጥናትና ድራማ በመጠቀም የሕግ አክባሪ  ሰው ባህሪያትን እንዲገልጹ (እነዲያንጸባርቁ) መግለፅ<br>♦ ተማሪዎች ሕግ አለማክበር በሚያስከትላቸው ችግሮች ላይ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ | ♦ ተማሪዎች ሕግ የማክበርን ምንነት እንዲገልፁ መጠየቅ<br>♦ ተማሪዎች ሲወያዩ ከምዕራፉ ከሚጠበቁ የመማር  ውጤቶች ጋር የተጣጣመ መሆኑን መከታተል<br>♦ ጥያቄና መልስ ማካሄድ<br>♦ ተማሪዎች የተጠየቁትን ሲመልሱ በመከታተል ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት<br>♦ ለተማሪዎች የቡድን ስራ መስጠት |

**ምዕራፍ 3፡ መልካም ስነምግባር** (የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት 20)

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡-

- ☞ ስለመልካም ስነ ምግባር ምንነት መግለጽ፤ይገልፃሉ
- ☞ መልካም ስነምግባር ያለው ሰው የሚያሳየውን ባህሪይ መዘርዘር፤
- ☞ ለመልካም ስነ ምግባር አስፈላጊነት ትልቅ ቦታ መስጠት፤
- ☞ የመልካም ልምዶች ማዳበሪያ መንገዶችን በተግባር ማሳየት፤
- ☞ የመልካም ስነምግባር አለመኖር የሚያስከትላቸውን ችግሮችር መለየት፡፡

| የትምህርቱ ውጤት | ይዘት | የመማር ማስተማር ዘዴ | ክትትል |
|---|---|---|---|
| ☞ የመልካም ስነምግባር ምንነትን መግለፅ<br>☞ መልካም ስነምግባር ያለው ሰው የሚያሳየውን ባህሪይ መዘርዘር፤<br>☞ ለመልካም ስነ ምግባር አስፈላጊነት ትልቅ ቦታ መስጠት<br>♦ የመልካም ስነምግባር ማዳበሪያ መንገዶችን በተግባር ማሳየት፤<br>☞ የመልካም ስነምግባር አለመኖር የሚያስከትላቸውን ችግሮች መለየት፡፡ | 3.1. የመልካም ስነ ምግባር ምንነት<br>3.2. የመልካም ሰው ባህሪ መገለጫዎች<br>3.3. የመልካም ስነምግባር አስፈላጊነት<br>3.4. የመልካም ስነ ምግባር ማጎልበቻ መንገዶች<br>3.5. መልካም ስነምግባር አለመኖር የሚያስከትለው ችግር | ♦ ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ ሆነው ስለ መልካም ስነ ምግባር ምንነት እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች በቡዝ የቡድን ዘዴ በመጠቀም የመልካም ባህሪ መገለጫዎች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፤<br>♦ ስለ መልካም ስነምግባርን አስፈላጊነት ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎችን አራት አራት አባል ባለው ቡድን በመከፋል የመልካም ስነምግባር ማጎልበቻ መንገዶች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች መልካም ስነምግባር አለመኖር የሚያስከትለውን ችግር እንዲያብራሩ ማድረግ፡ | ♦ ስለ መልካም ባህሪ ጥያቄና መልስ ማካሄድ<br>♦ ተማሪዎች ስወያዩ ከትምህርት ውጤቶች ጋር የተጣጣመ መሆኑን መከታተል<br>♦ ጥያቄና መልስ ማካሄድ<br>♦ የተማሪዎች ለተጠየቁት ጠያቄ መልስ ሲሰጡ በመከታተል ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት<br>♦ የሙከራ ፈተናዎችን ማስጠት |

**ምዕራፍ 4፡ በማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ** (የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት 20)

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡

- ☞ የማህበረ–ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ምንነትን መግለጽ፤
- ☞ የዜግነት (የበጎ ፈቃደኝነት) ተሳትፎ ያለውን ጠቀሜታ መገንዘብ፤
- ☞ በበጎ ፍቃደኝነት ስራ ውስጥ መሳተፍ፤
- ☞ የባህላዊ ፍርድ ቤት ምንነትን መረዳት፤
- ☞ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ለህብረተሰቡ በጋራ መኖር ያላቸውን ሚና ማድነቅ፤
- ☞ የህብረተሰቡን ችግር ለመፍታት የቡሳ ጎኖፋ ተቋም የሚጫወተውን ሚና መረዳት፤
- ☞ ቁጠባ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ሚና መለየት፤
- ☞ ታማኝ ግብር ከፋዮች በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያላቸውን ሚና መዘርዘር፡፡

| የትምህርቱ ውጤት | ይዘት | የመማር ማስተማር ዘዴ | ክትትል |
|---|---|---|---|
| ☞ የማህበረ–ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን ምንነት መግለፅ፤<br>☞ የዜግነት (የበጎ ፈቃደኝነት) ተሳትፎ ያለውን ጠቀሜታ ማድነቅ፤<br>☞ በበጎ ፍቃደኝነት ስራ ውስጥ መሳተፍ፤<br>☞ የባህላዊ ፍርድ ቤት ምንነትን መረዳት<br>☞ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ለህብረተሰቡ በጋራ መኖር ያላቸውን ሚና ማድነቅ፤<br>☞ የህብረተሰቡን ችግር ለመፍታት የቡሳ ጎኖፋ ተቋም የሚጫወተውን ሚና መረዳት፤<br>☞ ቁጠባ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ሚና መለየት። | 4.1. የማህበረ–ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ምንነት<br>4.2. የዜግነት (የበጎ ፈቃደኝነት) አገልግሎት<br>4.3. የባህላዊ ፍትህ አገልግሎት (ባህላዊ ፍርድ ቤት)<br>4.4. የህብረት ስራ ማህበራትን ማጠናከር (ቡሳ-ጎኖፋ)<br>4.5. የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን የሚያጠናክሩ ተቋማት (ግብር እና ቁጠባ) | ♦ ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ ሆነው ስለ ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ምንነት እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎትን አስፈላጊነት በድራማ መልክ እንዲያሳዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች ግብር መክፈልና ቁጠባ በማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ባላቸው ሚና ላይ እንዲወያዩ ማድረግ | ♦ ስለ ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጥያቄና መልስ ማካሄድ<br>♦ ተማሪዎች ስወያዩ ከትምህርት ውጤቶች ጋር የተጣጣመ መሆኑን መከታተል<br>♦ የተማሩትን በመጠየቅ ማወያየት<br>♦ ተማሪዎችየተጠየቁትን ስመልሱ በመከታተል ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት<br>♦ የቡድን ስራ መስጠት |

**ምዕራፍ 5፡ የሀገር ፍቅር** (የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት 19)

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡

- ☞ ስለ ሀገር ፍቅር ምንነት መግለጽ፤
- ☞ የሀገር ፍቅር መገለጫዎችን መዘርዘር፤
- ☞ የሀገር ፍቅር መላበስ አስፈላጊነትን መግለጽ፤
- ☞ የሀገር ፍቅር የተላበሱ ሰዎች የሚያሳዮቸውን ባህሪያት በተግባር ማሳየት፡፡

| የትምህርቱ ውጤት | ይዘት | የመማር ማስተማር ዘዴ | ክትትል |
|---|---|---|---|
| ☞ ስለ ሀገር ፍቅር ምንነት መግለጽ፤<br>☞ የሀገር ፍቅር መገለጫዎችን መዘርዘር፤<br>☞ የሀገር ፍቅር መላበስን አስፈላጊነት መግለጽ፤<br>☞ የሀገር ፍቅር የተላበሱ ሰዎች የሚያሳዩትን ባህሪያት በተግባር ማሳየት፡፡ | 5.1. የሀገር ፍቅር ምንነት<br>5.2. የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች መግለጫዎች<br>5.3. የሀገር ፍቅር አስፈላጊነት<br>5.4. የአገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ባህሪያት<br>5.5. ሀገርን መውደድ | ♦ ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ ሆነው በሀገር ፍቅር ምንነት ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች የሀገር ፍቅር መግለጫዎች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎችን አራት አራት አባላት ባሉት ቡድን በማዋቀር የሀገር ፍቅር ባላቸው –ዜጎችን ባህሪያት ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች  የአንድ አርበኛ ታሪክ ፈልገው ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች ለምን ሀገራቸውን መውደድ እንዳለባቸው ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ | ♦ ተማሪዎች የተማሩትን መጠየቅ<br>♦ የተማሪዎችን ተሳትፎ መከታተል<br>♦ የተማሪዎችን ተሳትፎ/ እንቅስቃሴ መመዝገብና ገንቢ ግብረመልስ መስጠት<br>♦ የክፍል ሥራ መስጠት |

**6፡ ሰላምና ህብረት** (የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት 19)

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- ☞ የሰላም ምንነት መግለጽ፤
- ☞ የሰላም አስፈላጊነትን ማብራራት፤
- ☞ መልካም ባህሪያትን ማድነቅ፤
- ☞ ስለ ህብረት ምንነት መግለጽ፤
- ☞ ለህብረት አስፈላጊነት ትልቅ ቦታ መስጠት፤
- ☞ የህብረትን እሴቶችን መለማመድ፤
- ☞ በሰላማና ህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት መለየት፡፡

| የትምህርቱ ውጤት | ይዘት | የመማር ማስተማር ዘዴ | ክትትል |
|---|---|---|---|
| ☞ የሰላምንና የህብረትን ምንነት መግለጽ፤<br>☞ ለሰላም አስፈላጊነት ዕውቅና መስጠት/ማብራራት፤<br>☞ የህብረት እሴቶችን መለማመድ፤<br>☞ ህብረት በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ያለውን ጥቅም ማሳየት<br>☞ በሰላምና በህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት መለየት | 6.1. የሰላም ምንነት<br>6.1.1. የሰላም አስፈላጊነት<br>6.2. ህብረት<br>6.2.1. የህብረት ምንነትና አስፈላጊነት<br>6.2.2. የህብረት እሴቶች<br>6.3. በሰላምና በህብረት መካከል ያለ ግንኙነት | ♦ ተማሪዎች በቡድን በቡድን ሆነው ስለ ሰላም ምንነት እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ የፒራሚድ ስልት በመጠቀም ተማሪዎች ስለ ህብረት እሴቶች እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች ስለ ሰላም አስፈላጊነት እንዲወያዩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ ሆነው የህብረት እሴቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ<br>♦ ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ ሆነው በሰላምና ህብረት መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲያብራሩ ማድረግ | ♦ ተማሪዎችን የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>♦ የተማሪዎችን ተሳትፎ መከታተል<br>♦ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በመመዝገብ ገንቢ ግብረመልስ መስጠት<br>♦ ማብራሪያ ወይም የሙከራ ፈተና መስጠት |